# ኢትዮጵያ

ጥቅምት/ህዳር 2007 3ኛ ዓመት



**ሀጎስ በዛብህ (በርሄ)**
ነባር የኢሕአፓና የኢሕአሠ አባል፤ የሰራዊት ኮማንደር በጀግነነት ሲዋጋ ተይዞ በቅርቡ በወያኔ በግፍ መገደሉ የታወቀ


**ርእስ አንቀጽ ገፅ 2**

ከትናንት - እስከዛሬ፤ የሰማዕታት ደም ይጣራል

የቀይ ሽብር ታሪክ በሰብአዊ መብት ቤተ መዘክር ውስጥ ሰፈረ

//

**ዜና ከተባለ ገፅ 3**

**ምን ይሰማ....... አገር ገፅ 3**

//

**ትላንትና ገፅ 5**

- በቀይ ሽብር የሞት ጥላ ሥር ፤የጓድ ቆንጂት ተክሉ ክራሞት

//

**ነፃ ሀሳብ ገፅ 6**

- መልኩ የእኒ፤ ግብሩ አረመኒ
- ብሄራዊ ችግር ያለ ሁሉም ትብብር አይወገድም


## ‘የወያኔ ወንጀለኛ ባለሥልጣናት የእጃቸውን ያገኛሉ!”

ኢሕአፓ

የቀድሞው የወያኔ ከፍተኛ ባለሥልጣን እና የትግራይ አስተዳዳሪ ፤ የአሁኑ አረና የተባለው ድርጅት መሪ ገብሩ አሥራት ፤ የኢሕአፓ አመራር አባላት የነበሩት እነ ጸጋዬ ገብረመድህን እና ነባር አባላቱ ከዘሬ 23 ዓመታት በፊት መገደላቸውን ይህንኑንም በቅርቡ በጻፈው መጽሐፉ መግለጹን ለአሜሪካ ድመጽ ሬዲዮ የአማርኛው ክፍል በሰጠው ቃለ-ምልልስ ገለጸ፡፡

እነዚህ ለሕዝባቸው እና ለሀገራቸው ራሳቸውን አሳልፈው በመስጠት አስከፊውን የደርግ አገዛዝ ሲታገሉ የነበሩ ብርቅዬ የሕዝብ ልጆች የተገደሉት ፤ በወያኔ ፍርድ መሆኑን ገብሩ አስራት ገልጿል። የሞት ፈርዱን የወሰኑትም ፤ ሟቹ መለስ ዜናዊ ፤ ስዬ አብርሃ ፤ ተወልደ ወልደ ብርሃን ፤ በረከት ስምኦን ፤ አባይ ጸሐዬ ፤ አለምሰገድ ገብረአምላክ እና ሀየሎም አርአያ መሆናቸው የታወቀ ሲሆን ፤ እሱ ግን በፍርድ ሂደቱ ላይ እንደሌለበት ተናግሯል፡፡

ይህንኑ ተከትሎ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ጠንከር ያለ መግለጫ ያወጣ ሲሆን ፤ መግለጫው “እነዚህ ወንጀለኞች ለፍርድ ቀርበው የእጃቸውን ማግኘት አለባቸው” ብሏል፡፡

ጸጋዬ ገብረመድህንን ጨምሮ ሌሎች ነባር የኢሕአፓ አባላት በወያኔ እጅ የወደቁት ፤ ወያኔ አዲስ አበባን ከመቆጣጠሩ በፊት ከሻዕብያ ፣ ከሱዳን እና ከሌሎች ባዕዳን አገሮች ጋር በመተባበር በኢሕአፓ ሠራዊት ላይ በከፈቱት ከፍተኛ ውጊያ ወቅት መሆኑ የሚታወስ ነው፡፡

## የኢምባሲዎቹ መደፈር የወያኔን አንገት አስደፍቷል

ከጥቂት ሳምንታት በፊት አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን በዋሽንግተን ዲሲ የሚገኘውን ፤ እንዲሁም በኖርዌይ የኢሕአፓ ወጣት ክንፍ ደርጅት(ኢወከንድ) አባላት እና ደጋፊዎች በስዊድን የስቶክሆልሙን የወያኔ ኢምባሲዎች ቅጥር ግቢዎች በመቆጣጠር የፈጸሙት የጀግንነት ተግባር ፤ ወያኔን እና የወያኔ ደጋፊዎችን አንገት ያስደፋ ፤ የተቃዋሚ ወገኖችን ደግሞ ያስደሰተ እና ያነቃቃ ለመሆኑ ወያኔ እያደረጋቸው ካሉ ከንቱ መወራጨቶች ለመረዳት ይቻላል፡፡ በተለይ ፣ በተለይ ዋሽንግተን የሚገኙ አገር ወዳዶች ፤ ኢምባሲው ቅጥር ግቢ ውስጥ ተሰቅሎ የነበረውን እና ኢትዮጵያን የማይወክለውን ባንዲራ አውርደው እውነተኛውን አረንጓዴ ፣ ቢጫ ፣ ቀይ ባንዲራ ለመስቀል የደረጉት ሙከራ እና ኢምባሲውን በተቆጣጠሩ ወገኖች ላይ ሽጉጥ የተኮሰው የወያኔ ነፍሰ ገዳይ ተይዞ በሀያ አራት ሰዓት ከአሜሪካ ምድር እንዲባረር መደረጉ በወያኔ ላይ ከፍተኛ የሞራል ድቀት እና ሽንፈት እንዳደረሰበት በግልጽ የሚታይ እውነታ ሆኗል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ኖርዌይ ውስጥ የሚገኙ የኢሕአፓ ወጣት ክንፍ አባላት እና ደጋፊዎች በተመሳሳይ ሁኔታ በሲውድን የሚገኘውን የወያኔ ኢምባሲ ለአንድ ሰዓት ገደማ ተቆጣጥረው ፤ በወያኔ ታፍነው የገቡበት ስለማይታወቀው የኢሕአፓ ልጆች የት እንደሚገኙ አምባሳደሯ ምላሽ እንድትሰጣቸው ያደረጉት ግብ ግብ እና ጥረት ፤ ምንም እንኳ ወያኔ በተለመደ ዝምታው ሁኔታውን ለማድበስበስ ቢሞክር እንዲሁም ነጻ ፕረስ ነን የሚሉትም ሁኔታውን ለመዘገብ ፈቃደኛ ባይሆኑም ፤ ድርጊቱ ለወያኔ ከፍተኛ እራስ ምታት እና ድርብ ሽንፈት እንደሚሆንበት የሚያጠራጥር አይደለም፡፡ ወያኔ ፣ እነዚሁ የተቃዋሚ ወገኖች ኢምባሲውን በቁጥጥር ስር ባዋሉ ማግስት ደጋፊዎቹን እና በገንዘብ የገዛቸውን ሆድ አደሮች በአሜሪካ ስቴት ዲፓርትመንት ፊት ለፊት አሰልፎ ፤ ባንዲራውን ከኢምባሲው ቅጥር ግቢ ውስጥ ለማውረድ የሞከሩትን ኢትዮጵያውያን ወገኖች ለማውገዝ መሞከሩ ፤ እንዲሁም ለማጭበርበር ፣ ‘’የባንዲራ ቀን’’ እያለ በየአመቱ በሚያከብረው ቀን በእነ ሬድዋን ሁሴን የተደራጁ እና አበል የተከፈላቸው ግለሰቦች ተሰባስበው አዲስ አበባ ውስጥ በሚገኘው የአሜሪካ ኢምባሲ ፊት ለፊት ተሰልፈው ፤ ‘’የኢትዮጵያን ኢምባሲ ያወኩ እና ሰንደቅ ዓላማችንን ያወረዱ ሰዎች ለፍርድ ይቅረቡ’’ የሚል ጥያቄ ማቅረባቸው ፤ ወያኔ የደረሰበትን ሽንፈት ለመቋቋም እና አንገት የደፉትን አባላቱን አና ደጋፊዎቹን ተስፋ እንዳይቆርጡ ለማበረታታት ያደረገው ለመሆኑ ብዙ ወገኖች ይስማማሉ፡፡



የወያኔ ባንዲራ ሲወርድ

ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## ለደብተራው (ጸጋዬ ገ/መድኅን)

ከጌትነት



መናገር ቢያቅተኝ፣ ምን አፌ ቢለጎም፣
በጊዚያዊ ብሽቀት፣ ተስፋዬ ቢጨልም፣
መኖርህን ነው እንጂ፣ መሞትህን አላልም!
ድንጋይ ሰብሮ ሩጫ፣ አወይ የጊዜ ቅል፣
ደብተራውን ገድሎ፣ በዘር መቀማጠል!?
አወይ የኛ ትውልድ፣ ወይ ዲሞክራሲ?
ወያኔ አራት ኪሎ፣ ደብተራው "ፈላሲ!"
በሰፈሩት ቁና፣ መሰፈሩ ላይቀር!
እድገት ልማት ብሎ፣ ከንቱ መቀባጠር!
እነርሱም ይግደሉ! እኛም እንሞታለን!
የነርሱ ግን ትቢያ! እኛ እናብባለን!
አቤ ኮሚሳሩ! ሥራህ ፈክቶ አብቧል!
ስጋህን በሉ እንጅ! መንፈስህ መች ሞቷል!
ተከታይ ልጆችህ፣ በረድፍ ቆመናል!
ምን ምስጥር ቢያደርገው፣ ለአሥርታት ደብቆ!
ፈራጁ ይከፍላል፣ በአዲስ ፈራጅ ታንቆ!
አንተ ያስተማርከው፣ ሆዱን ካስቀደመ!
ነጻነቱን ሸጦ!
ባርነቱን ይምረጥ፣ ሁሉም ተርመጥምጦ!

አክቶበር 15. 2014



የኢትዮጵያ ጋዜጣን በተለያዩ ድረ ገጾች

EPRP.COM
ASSIMBA.ORG
DEBTERAW.COM
ETHIOLION.COM
ወዘተ.

- FACE BOOK (ethiopianewspape

# ኢትዮጵያ

**በኢሕአፓ የዲሲና አካባቢዉ ደጋፊ አካል**
**የሚዘጋጅ ወራዊ ጋዜጣ**

አድራሻ፡ 5309 Georgia Ave. NW 2nd floor Washington DC. 20011
ስ/ቁ፡ 202 291 4217
ኢሜል፡ dc..region.eprp@gmail.com

## ርዕሰ አንቀጽ

## ከትናንት - እስከዛሬ፤ የሰማዕታት ደም ይጣራል

ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ክብርና ለሕዝቧ ነጻነት እስከዛሬ ድረስ በተደረጉት ትግሎች በህይወት የተከፈለዉ ዋጋ እጅጉን ከፍተኛ ነዉ ። በቅርቡ ዘመን ታሪካችን ዉስጥ በዘግናኝነቱ ምኔም ላይረሳ በሰፈረዉ የ "ቀይ" ሽብር የጽልመት ዘመን እንኳ ለሀገሩና ለወገኖቹ መልካም ህልም የነበረዉ አንድ ትዉልድ ተመትሯል ። ገዳዮችንና በሰዉ ስቃይ የሚደሰቱ በላዔ ሰብ ፋሺስቶችን በአዋጅ በማሰማራት የሀገሪቱን ወጣቶች ያረደዉ የደርጉ ወታደራዊ አገዛዝ ተገርስሶ ከወደቀ ሀያ ሶስት ዓመታት ቢቆጠሩም ምድሪቱን በደም አበላ የነከሩት ግፈኞችና የወንጀል ግብረ አበሮቻቸዉ እስከዛሬ ከፍትህ አደባባይ ቀርበዉ የዘሩትን እንዲያጭዱ አልተደረገም ። ለይስሙላ በተቋቋመ ችሎት የቀረቡት የአገዛዙ ቁንጮ ባለሥልጣናትም ቢሆኑ ፤ ያፈሰሱት ደም የሰዉ ያልነበረ ያህል ነጻ ተለቅቀዉ በመፏለል ላይ ይገኛሉ ። የሰማዕቶቻችን ደም ዛሬም ለፍትህ በመጮህ ላይ ነዉ ።

ይህ ያለፈ - የተዘነጋ ሁኔታ ከቶ አይደለም ። ያለፈዉን ሁሉ በተዘጋ ፋይል ዉስጥ አጉረን በኢዮብ ትዕግሥት እንለፈዉ የሚሉ የዋሀን ፤ ግፈኞች ከሕግ አደባባይ ቆመዉ የሚዳኙበት ሥርዓት እስካልተፈጠረ ድረስ ፤ የሕዝብ ትከሻ ምን ያህል ቢላጥ ፤ ግፈኞችን እያፈራረቀ ከመሸከም የሚገላግል አንዳች መፍትሔ እንደማይገኝ ሊገነዘቡት ሁኔታው ግድ ይላቸዋል ። በዚህ ረገድ ፤ የቀድሞዉ የወያኔ አመራርና የአገዛዙ ባለሥልጣን የነበረዉ ገብሩ አሥራት ፤ ከሁለት አሥርት ዓመታት በላይ ካስቆጠረ ድብብቆሽ በኋላም ቢሆን ፤ ይፋ ያደረገዉ እዉነት ሊጠቀስ የሚገባዉ ማሳያ ነዉ ። የመንግሥቱ ኃ/ማርያም አምባገነናዊ አገዛዝ የጨፈጨፋቸዉ የኢሕአፓ ሰማዕታት ያረፉበትን የጅምላ መቃብሮች በመኀድፈር የባጀዉ ወያኔ በታላቁ ምንሊክ ቤተ መንግሥት ከመደላደሉ አስቀድሞ ከእጁ የወደቁትን ፤ ጻጋዬ ገብረ መድህንን ( ደብተራዉን ) እና ሌሎች የኢትዮጵያ አብዮታዊ ፓርቲ ከፍተኛ የአመራር አባላትንና ተዋጊ ጓዶችን ከሕግ ጋር ከቶ በማይተዋወቅ ድርጅታዊ ዉሳኔዉ ጭዳ አድርጓቸዋል ። ባመኑበት መስመር ሲታገሉ የተሰዉት የነዚህ መሪዎችና የሕዝብ ልጆች በድን የወደቀበት ሥፍራም እስከዛሬ ድረስ አይታወቅም ።

ጻጋዬም ሆነ የተቀሩት ጓዶቻችን በወቅቱ ከፋሽስታዊዉ የደርግ አገዛዝ ጋር ሲደረግ በነበረዉ የብረት ትግል ፤ በኢሕአፓ መሪዎች ባህል መሠረት የግንባር ሥጋ ሆነዉ ለሕዝባችን ነጻ መዉጣት ፤ ገና በአፍላ ዕድሜአቸዉ የጀመሩትን ትግል ቀጥለዉ ፤ ከመፋለም ዉጭ የፈጸሙት አንዳችም ወንጀል አልነበረም ። በወያኔዎቹ ጸረ ሕዝብ የጫካ ችሎት ከወንጀል ተቆጥሮ በጭካኔ ያስገደላቸዉ ጉዳይ ቢኖር የኢትዮጵያን አንድነትና ብሔራዊ ጥቅምና የሕዝባችንን የሥልጣን ባለቤትነት ለድርድር ላለማቅረብ እነርሱም ሆኑ ድርጅታቸዉ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ ) የሚያራምዱት ጥብቅ አቋም ብቻ ነዉ ። በዚህ ረገድ ግድያዉ የወያኔን እኩይ ጸረ ዴሞክራሲ ተፈጥሮና የማይመከር ጸረ ኢትዮጵያ ተልዕኮ ይበልጥ ርቃን አዉጥቶ ከማሳዬት ወዲያ የሚፈይደዉ አይኖርም ። ኢሕአፓም ሆነ ሰማዕታቱ ጓዶች የተሸከሙትን ሕዝባዊ ኃላፊነት ክብደትና በትግሉም ሂደት ዉስጥ የሚገጥማቸዉን ፈተና ብርታት ገና ከጧቱ ጠንቅቀዉ የተገነዘቡ መሆኑን እንኳንስ ሕዝባችን ወያኔ ራሱ ጠንቅቆ የሚያዉቀዉ ዕዉነት ነዉ ። ትግሉም ቢሆን የሕዝቡ የሥልጣን ባለቤትነት እስኪረጋገጥና በኢትዮጵያ ዉስጥ ፍትህ እኩልነትና ዴሞክራሲ እስኪሰፍን ድረስ ለአፍታም ያህል የማይቆም ስለመሆኑ ጥርጣሬ ሊኖር አይገባም ። በትግሉ መስክ የወደቁትን ጓዶች ሰንደቅ በመሸከም ትግሉን ዳር ለማድረስ "በናንት የአመጽ መንገድ፤…" ዝማሬ ትግሉን ማቀጣጠል የኢሕአፓዎች ሁሉ ነባርና ቀጣይ ትዉፊት ነዉ ።

በጻጋዬ ደብተራዉና በሌሎቹም ሰማዕት ጓዶቻችን ሕይወት ላይ ከለየላቸዉ ጸረ - ኢትዮጵያ ኃይሎች ላረፈዉ የፍርሀት በትር ፤ ኢህጋዊዉን የጫካ ዉሳኔ ካስፈጸሙት የወያኔ ግፈኛ መሪዎች አንስቶ ከሰብዐዊነት ዉጭ የተፈጸመዉን ይህን ታላቅ ብሔራዊ ወንጀል በመደባበቅ ረገድ ትብብር እስካደረጉላቸዉ ጸረ ሕዝብ ኃይሎች ድረስ የሚሰደሩት ሁሉ ከተጠያቂነት አያመልጡም ። ዛሬም ቢሆን ከተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች ተይዘዉ በወያኔ እጅ የወደቁና ደብዛቸዉ የጠፋ አያሌ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ ) ታጋዮች መኖራቸዉም ለአንዳፍታም ቢሆን ሊዘነጋ አይገባዉም ። መዳረሻቸዉን ማፈላለጉ ተደራቢ ግዳጃችን ነዉ ። መሥዋዕት ሆነዉ የወደቁት ጓዶቻችን በድን ከወዳደቀበት ቦታ ተነስቶ በክብር እስከሚያርፍበት ሕዝባዊ የድል ዕለትም ትግላችን ይቀጥላል ። ክብር ሞቱ ለሰማዕት/

ሕዝባዊዉ ዴሞክራሲያዊ ትግል ያቸንፋል //
በነጻነቷ ኮርታ ፤ ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር//

## የቀይ ሽብር ታሪክ በሰብአዊ መብት ቤተመዘክር ውስጥ ሰፈረ

ከሶሴፐ ሰሜን አሜሪካ ተወካይ የቀረበ ዘገባ

ቀይ ሽብር በኢትዮጵያ ቀርቶ በየትኛውም አገር ሕዝብ ላይ እንዳይደገም ኢትዮጵያውያን ደግመን ደጋግመን የማስተማርና የመሟገት ሃላፊነት አለብን፡፡ በዊኒፔግ ካናዳ የተገነባው የሰብአዊ መብት ቤተመዘክር ለበርካታ ጎብኝዎች በተለይም ለወጣቶች የሚሰጠው ግንዛቤ እጅግ በጣም ከፍተኛ ነው፡፡ አንዳንድ የዋሆችና በርካታ የቀይ ሽብር ፈጻሚዎች "ቀይ ሽብር ያለፈ ጉዳይ ነው፡፡ የሞተን ነገር መቀስቀስ ነው፡፡" ሲሉ ይደመጣሉ፡፡ የዋሆቹ "የሞኝ ልቅሶ መልሶ መልሶ" ሆኖባቸው ነው፡፡ ባለቀይ ሽብሮቹ ግን ጉዳቸው እንዳይታወቅ ለመሸፋፈን ነው፡፡ ቀይ ሽብር አስከፊ ታሪካችን ነው ተቀበልነውም አልተቀበልነውም፡፡ ታሪክ ደግሞ ታሪክ ነውና ሲነገር ለዘላለም ይኖራል፣ የቀይ ሽብር አራማጆች ሞተዋል፡፡ ያሉትም እድሜያቸው ሲያበቃ ይሞታሉ ውርደትንና እፍረትን ተከናንበው፡፡ የቀይ ሽብር ታሪክ ግን ዘላለማዊ ነው፡፡ ግማሽ ሚሊዮን ብርቅዬ የኢትዮጵያን ልጆችን ያጨደው ቀይ ሽብር የካናዳውያን የሰብአዊ መብት ቤተመዘክር ምስጋና ይግባውና ለዘላለም ከአለም አካባቢ በሚመጡ ሕዝቦች ይጎበኛል፡፡ ቀይ ሽብር ልክ እንደ ሆሎኮስቱ እልቂት ዳግም መፈጸም የለበትም የሚለውን ትምህርት ሲያስተምር ይኖራል፡፡ ትውስታው ለማስተማር እንጅ ብቀላን ለማካሄድ አይደለም፡፡ በርግጥ ፋሺስቱ መንግስቱ ሃይለማሪያምና ቱባ ቱባ የቀይ ሽብር መሪ ተዋንያኖቹ ከፍትህ ፊት መቆማቸውና ፍርዳቸውን ማግኘታቸው አይቀርም በቅድሚያ ካልሞቱ በስተቀር፡፡
ባለፈውና ባሁኑ ሳምንት በካናዳ የዊኒፔግ አየር በሰብአዊ መብት ተከራካሪው አሊ ሁሴንና በቀይ ሽብር ትውስታ ተጨናንቆ ከርሟል፡፡ አሊን ያየ አላፊ አግዳሚው ቆም ብሎ "ይህን ታሪክ ሕዝቡ እንዲያውቀው በማድረግህ ከልብ አመሰግናለሁ" ሲሉት ለማየት በመብቃቴ የተሰማኝ ደስታ ልዩ ነው፡፡ ቀይ ሽብር ከግማሽ ሚሊዮን በላይ ሕዝባችንን በልቷል፡፡ የሆሎኮስት ታሪክ ሲነሳ ፋሺስቱ ሂትለር መነሳቱ የግድ ይላል፡፡ የኢትዮጵያው ቀይ ሽብር ሲነገር ፋሺስቱ መንግስቱ መነሳቱ ተገቢ ነው፡፡




የዊኒፔግ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን የሆነችው የቅድስት ማርያም ደብረገነት አስተዳዳሪ አባ ፍቅረስላሴ ጸጋው፣ የአሊ ሶስት ልጆቹ (ምሳሌ፡ ሃኪምና ኦሪት) የልጅ ልጁ ቃለአብና ባለቤቱ ያይኔ፣ የሰሜን አሜሪካ ሶሴፐ ተወካይ የተሰጠንን የክብር እንግድነት በመቀበል ልክ ከጠዋቱ በ፲ ሰዓት ከቤተመዘክሩ ዋነኛ መግቢያ በር ላይ ደረስን፡፡ አሊ ስለአባ ፍቅረስላሴ ሆነ ስለ ቅድስት ማርያም ደብረገነት ቤተ ክርስቲያን ያለው ከበሬታ ከፍተኛ ስለመሆኑ ደግሞ ደጋግሞ በፍቅር ሲያነሳቸው ሰምቻለሁ፡፡ አባና ቤተ ክርስቲያኒቷ ከሱዳን፣ከኬንያ፣ ከዑጋንዳ፣ በርካታ ስደተኞችን ተቀብለው አስተናግደዋል፡፡ ስለ አባ ታላቅነትና ግሩም ስራ ካለሁበት ሃገር ቀደም ሲል ሰምቻለሁ፡፡ ታሪካዊ በሆነው የዊኒፔግ መሃል ከተማ ጥግ ዘለቅና ቀጥ ብሎ በኩራት የተንጣለለው የካናዳውያን የሰብአዊ መብት ሕንፃ ነው፡፡ ከአናቱ ላይ ቀጥ

ወድ ገጽ 7 ዞሯል

# ዜና ከተባለ

**መሰተዋት ከድሬ**

### "ነገረኛ ያገር ልጅ የጠላቶቹ ባርያ ይሆናል"

ዜናማ ሞልቷል--የጠበቅነውም ቢሆን የሚያስቆጣ፤ የሚሳዝን፤የሚያበረታታና የሚያስቅም ። ፈሪው ወያኔ በእስር የያዛቸውን የኢሕአፓ አመራር አባላትና አንጋፋ ታጋዮችን ራሱ መንግስት በሚለው የፍትህ ፍርድ ቤት እንኳን ሳይቀርቡ (ለነገሩ በወያኔ እጅ የወደቀ ኢሕአፓ ለየትኛው ፍርድ ቤት ቀርቦ ያውቃል?) በዚያው በግፍ በትግራይ ገድሏል ። ይህን ወንጀል የፈጸሙትና ያስፈጸሙት ጊዜቸውን ጠብቀው ዋጋ መክፈላቸው ከቶም የማይቀር ነው ፡፡ የኢትዮጵያ ብርቅ ልጆችን በመረሸኑ ወያኔ ተቸናፊነቱን ፈሪነቱን እንጂ ሌላ አላሳየም ። የባሰው ደግሞ የወያኔ ተቃዋሚ ነን የሚሉት ሳይቀሩ ይህን ወንጀል በማውገዝ ፈንታ ዝምታን መምረጣቸው ነው ። ይህም ሌላ ትዝብት ነው።

ኦነግ የተባለውን ድርጅት ወደ ቀና መስመር ሊመልስ ተነስቷል ሲባልለት የነበረው ጄኔራል ከማል ገልቹ ይመራዋል የተባለው የኦነግ አንጃ ከሊቀመንበርነት ክስ በክስ ደርድሮበት አስናብቶታል ። ተኪም ይመደብለታል ተብሏል። ግለሰቡ ከአስመራ መውጣቱ ይፈይድለታል ወይስ የኮሎኔል ታደሰ ዕጣን--መታሰር መሰወርን- ይቀበላል የሚለው ብዙዎች በጉጉት እሚጠብቁት ዜና አይደለም ። በሌላ በኩል ደግሞ አዲስ ቡድን ፈጥረናል ሲሉ የቆዩት እነ ዲማ ነገዎ ወደ አዲስ አበባ አቅንተዋል። ቢያንስ በመጀመሪያ ዲማ ደርሷል--ሌንጮ ይከተላል ። ይህ የዲማ አዲስ አበባ መግባት ግን አነጋሪ ዜና ሆኖ አለመገኘቱ ራሱ የእነ ዲማ የመጪው የወያኔ ምርጫ ሽፋን ሰጪነት ሚናም ገለባ መሆኑን የሚገልጥ ነው የሚል ግምገማን አስከትሏል ። እነ ዲማን ከወያኒ አስታራቂ ሆኖ የተገኘው ያ የለመደበት የሽማግሌ ቀላል ፕሮፌሰር ኤፍሬም ይስሓቅ መሆኑም ታውቋል ።ሌሎችም በተመሳሳይ መልክ ወደ ወያኔ ሊነጉዱ ቢፈልጉም ቂመኛው ወያኔ እስካሁን አልጋብዝ ብሎ አሳፍሯቸው ይገኛል ። የአገው ተወላጅ ነኝ ባዩም የወይኔ ጀኔራል አበባው ታደሰ ከመከላከያ በአጠቃላይም እንዲሰናበት መደረጉ ወያኔ ራሱን ብአዴን በሚለው ተለጣፊ ቡድን ላይ ያለውን ፍጹም የበላይነት ያሳይል ሲሉ ታዛቢዎች ጠቁመዋል ። ጄኔራሉ በመጠኑ በማንገራገሩ ቀደምም ተንሳፎና ተሸሮም እንደነበር የሚታወስ ነው ። በዚህም በዚያም ግን ጀኔራል ተብዬዎቹ በአብዛኛው ችሎታ ቢስ የክልል አንድ ተወላጆች መሆናቸው ቁልጭ ብሎ የሚታይ ነው ።

በአማራው ሕዝብ ላይ ወያኔ ያለውን መራራ ጥላቻ በገሀድ ካወጣ ዓመታት ያለፉ ቢሆንም ስልጣን ከያዘ በኋላ ባሰበት እንጂ አልቀነሰም ። በመሆኑም አማራ ምንጠራ በሚል በደቡብና በጋምቤላም በተካሄደ ፍጅት ከ500 ሰው በላይ መገደሉ ተዘግቧል ። የወያኔ ፖለቲካ እምብርቱ አልን ማዕከሉ ጸረ አማራነት ነውና አማራውን ማዋከብ፤ማፈናቀል፤መግደል፤ ሞራሉን ማድቀቅ፤መከፋፈል' መሬቱን መንጠቅ፤ ለቀሳፊ በሽታ መዳረግ ወዘተ የወያኔ ተልዕኮ ሆኖ ቆይቷል። የተለወጠ የለም--ባስ እንጅ እንዲያውም ። ይህን በህዝብ ላይ የመጣ ፍጅት ከመቃወም አንጻር የታየው እንቅስቃሴ የሚያመረቃ አለመሆኑም ግልጽ ነው ። በሱዳን፤በመካካለኛው አፍሪካ፤ ወዘተ ግድያ ደራ ብለው አነባን የሚሉት ባዕዳን ደግሞ ሰለ አማራው መፈጀት መተንፈስም አልፈለጉም ። የየሀገሩን የፖለቲካ ሁኔታ ጠንቅቀን እናውቃለን ባዩ የተባበሩት መንግስታት ሻዕቢያን አጋለጥኩ ባለበት ዘገባ ግንቦት 7 እንቅስቃሴ በአማራ ምሁሮች ምርጦች የተቋቋመ ነው ብሎ መዘገቡን እንደ ምሳሌ ማንሳት ይቻላል ። ፖል ሄንዚና ጆን ፔንደርጋስት ለምሳሌ ወያኔን የሚቃወሙት ወይ የደርግ ርዝራዦች አሊያም የአማራ ትምክህተኞች ናቸው ብለው ሲጽፉ ሲለፍፉና አማራውን ለወያኔ ሲሉ ሲያጠቁ ነበር ። ባዕዳኖችም ልክ ኢሳያስ ይል እንደነበረው የኢትዮጵያ አንድነትን ለማጥቃት አማራውን መነጠልና መምታት የሚሉ ናችውና (ለሀገር አንድነት ሁሉም ሕዝብ ያልታገል ይመስል!) የአማራው መከራ ከኢትዮጵያ ሰቆቃ ጋር የተያየዘ ነው ። ነውናም ዜጎች በሞላ ይህ በአማራውው ላይ እየደረሰ ያለውን ፍጅት (በ ኦጋዴንም፤ በጋምቤላም ወዘተም) መቃወምና ከተጠቃው ሕዝብ ጋር አብሮ መቆም አለበት። ወያኔ በለስ ቀንቶት ዓለም አቀፍ ሽብር የሚል ስለመጣለት የኢትዮጵያን መሬት ለአሜሪካ ጦር ሰፈርነት ሰጥቶ-- አስደፍሮ፤ ወታደር በዋሺንግተን ትዕዛዝ ወደ ሶማሊያ ልኮ እያስጨረሰ ዋጋውን ከፍ አድርጎ የባዕዳኑን ድጋፍ አግኝቷል ። በፋሽስቱ መንግስቱ ሀገራችንም ደቃና ተዳክማ ያገኘው ወያኔ መግዛቱም ሆነ መከፋፈሉ ቀሎታል ማለትም ይቻላል። ዋልጌነትን አስፋፍቶ፤ ለአቅመ ሔዋን ያልደረሱትን የካድሬና ባለስልጣናት መጫወቻ አድርጎና ለዘመናዊ ባርነትም ሸጦ፤ህጻናትን በገንዘብ ለጉዲፈቻ ቸብችቦ ፤ድህነትና ዘረኝትን አስፍኖ ባለበት ባእዳን ኤኮኖውን አሳደገ እያሉ መቀባጠራቸው አላቆም ብሎ አለ ። ሌሎች ቦታዎች ይቅርና በአዲስ አበባ ራሷ መብራት፤ውሀ ጠፍቶ እያለ ይህ የሚለፈፍ ዕድገት የትና ለማን እንደሆነ ሕዝብ ግን አላጣውም ። የወያኔ ፕሬዚዳንት ተብዬ በዋሾዎች ዋሻ ገብቷልና ሲቀላምድ ግልገል ጊቤ 3 ሲያልቅ ሁሉ ቦታ መብፋት ይዳረሳል ብሏል ። የደበቀው ሀቅ ግን አሁን ባሉት ግድቦች የሚመነጨው ሀይል ለመላ ኢትዮጵያ በቂ መሆኑን ነው ። የመብራት መጥፋት ከወያኔ ሙስናና የስርጭቱን ኮንትራት/ስራ በጉቦ ለቻይና መስጠቱ ጋር ይተያያዘ ነው ። መብራት ሀይል በሌለበትና ውሀ በጠፋበት ሀገር ኤኮኖሚ ሲያድግ ሲመነደግ የሚታየው ለወያኔና ለጡት አባቶቹ ብቻ ነው ።

ወያኔ ገንዘብ ሊያጠፋና ራሱን ሊደልል ስልጠና የሚል ፈሊጥ አምጥቶ ተማሪ፤አስተማሪ፤ ቢሮ ሰራተኛ ፖለቲከኛውን ሁሉ ስልጠና እሰጣእሁ ብሎ እንኳን ሊያስተምሩ ራሳቸው ወደ ጀማሪ ትምህርት ቤት መግባት ያለባቸውን ካድሬዎቹን ለሰልጣን ብሎ ፤ስልጠናውም የግድ ነው ብሎ ደንግጎ ጊዜ ሲያጠፋ ባጅቷል። የስልጠናው ትርኪ ምርኪ የወያኔ የቅጥፈት ሰነድ መሆኑ ማንም አላጣውም ። ቀደም ሊያሰራጭ ሞክሮ የከሸፈበትን ጸረ ኢሕአፓ ቅጥፈት ለምሳሌ ዳግም ሀቅ ብሎ ሊለቀው በዚህ ስልጠና ሰነዱ ሞክሯል ። የስልጠናው ሂደት የጠቀመው አበል ለሚያገኙትና አሰልጣኝ ተብለው ገንዘብ ለሚያፍሱት ብቻ ነው ። ወያኔ ግን በራሱ ውሸት መፈንጠዝ ያውቅበታልና የዩኒቨርስቲ አስተማሪዎች ሳይቀሩ ተጠቅመን ብለው ገለጡ እያለ ያሾፋል ። በግርግሩ ብዙ ሚሊዮን ብር (ከ 200 ሚሊዮን ብር በላይ ይላሉ አንዳንዶች) ሸው ብሎ ጠፍቷል ። ያ አንዳንድ ሞኞችን ያታለለ ቦንድ ተብዬ መሳለቂያም የገባው በወያኔ አገዛዝ ወጪ ሆኗል ሲሉ ታዛቢዎች ገልጠዋል ።በጉባ አካባቢ ትልቅ ግድብ ተብሎ የተጀመረውም ዳዴ እያለ መሆኑን ወያኔ ሊደብቅ አልቻለም ።

**እስቲ የሚከተሉትን በግንዛቤ እንያዛቸው፡**

- ዘጠኝ በሀገር ውስጥ ያሉ ድርጅቶች (ሰማያዊ ፓርቲና መኢሕድን ጨምሮ) ለመጭው የወያኔ ምርጫ አንድ የተባበረ እንቅስቃሴ ለማድረግ መስማማታቸውን ገለጹ፤
- የኢትዮጵያ የፖለቲካ አስረኞች አንድነት ኮሚቴ የእነጺጋዪን በግፍ መገደል አንስቶ አሁንም ቢሆን የደረሱበት ያልታውቀ እነ አበራሽ በርታ፤ተስፋዬ ከበደ፤ሞት ባይኖር፤ ብርሃኑ እጅጉ፤ ታምራት (ሙቶቶ)፤ አበበ ዓይነኩሉ፤ወንዲሲራክ ደስታ፤ኢዮብ ተቀባ፤ደምሴና ሌሎችም እንዳሉ መዘንጋት የለብንም ብሏል ።
- የወያኔ ጥብቅ ወዳጅ የሆነው የእንግሊዝ ጠቅላይ ሚኒስቲር ለወያኔው ጠቅላይ ሚኒስቴር ተብየ የአንዳርጋቸው ጽጌን መታገት አስመልክቶ ደብዳቤ ጽፌያለሁ ቢልም (በአንዳርጋቸው ባለቤትና ልጆች ጥያቄ መሰረት) ምን እንደጻፈና ምን እንደጠየቀ ግልጽ የሆነ ነገር የለም ። እንግሊዝ የአንዳርጋቸውን መጠለፍ ሳታወግዝ ሞት ፍርድ እንዳይፈጸምበት ብቻ ብላ መግለጫ በመስጠቷ በወንጀሉ ተካፋይ ናት ተብላ ስትታማና ስትወገዝ መክረሟም ድብቅ አይደለም ።
- ደቡብ ሱዳን በአዲስ አበባ ያለውን አምባሳደሯን ተመልስ ብላ ጠርታው እያንገራገረ ነው ተብሏል። ከዚ በፊት ሌላ አምባሳደር ተጠርቶ ከተመለሰ በኋላ ደብዛው ጠፍቷል ያሉት ታዛቢዎች ይህኛውም የአማጺው የሪያክ ማሻር ጎሳ (ኑዌር) በመሆኑ ምስጢርን ለአማጽያኑ አቀብሏል የሚል ክስ አለበትም ተብሏል ።
- ወግ ወጉ ተይዟል በተባለው መሰረት ወያኔ የኢትዮጵያ ሕዝብ የጤና ይዞታ ብልሽትሽት አድርጎ (ገዢው ክፍል የሚታከመው ታይላንድ ተጉዞ ነው ) ለወጉ ያህል ወደ 200 የጤና ባለሙያዎችን ወደ ምዕራብ አፍሪካ ኤቦላን እንዲዋጉ ልልክ ተነስቻለሁ ብሎ ሕዝብን እያሳቀው ነው ።
- ከወያኔው ስብሓት ነጋ ጋር ይሰራል ተብሎ ሲታማ የቆየ አንድ ጋዜጠኛ (ከ1997 ብቅ ካለበት ጊዜ ጀምሮ አንዴም ታስሮ ባለማወቁ) ሰሞኑን ወደ ጣቢያ ተጠርቶ መያዙ ምናልባትም የነበረበትን ሐሜት ለመሸፋፈን ነው የሚል ጥርጣሬ ተናፍሷል ። ልደቱ ክህደቱስ ለወር ወደ ዝዋይ ወርዶ አልነበር? ሸፋን መስጠት ይባላል ።

## ምን ይሰማ……አገር?



**" .....የተፈረደብኝን ቅጣት ጨርሼ ያለአንዳች ምክንያት ህገ መንግሥቱን በመጣስ እስከዛሬ ነሐሴ ፲፯ ቀን ፪፻፯ ዓ.ም ድረስ ፻፲፰ ቀናት ወይም ሁለት ሺህ ሰባት መቶ ስድሳ ሰዓታት ታግቼ እገኛለሁ ።"**

*(የጎንደሩ አራጅ ሻ/ቃ መላኩ ተፈራ ለወያኔዉ ጠ/ ሚኒስትር የጻፈዉ የ"ልፈታ" አቤቱታ ዋና ሃሳብ ፤ ኢሳት ሬድዮ መስከረም ፯ ቀን ፪፻፯ ዓ.ም እንዳስደመጠዉ ።)*

- በግብር ካንተ ለማይበልጡ ሰዎች ማመልከቻ በመጻፍ ጊዜህን አታባክን ። ይልቁኑ ፤ ፈጠን ብለህ " ጽሑፍ" ጻፍላቸዉ ። ኢሕአፓን " እንዳይሸጥ - እንዳይለወጥ " አድርገህ ሞልጨህ መጽሐፍ ካሳተምክ ራሳቸዉ ከፍለዉ ይፈቱሃል ። ከዚያም እንደፋሺስቱ አቻህ እንደግራዚያኒ ከተወለድክበት መንደር ዉስጥ ሐዉልት ያቆሙልሃል ።

//

**"ፑንትላንድና ሶማሌላንድ ከኢትዩጵያ ጋር የመዋሃጃ ሰነድ አቀረቡ ፤- ሰነዱ አሜሪካንን ጨምሮ ለኃያላን አገሮች ቀርቧል ።"**

*(ጎልጉል የድረ ገጽ ጋዜጣ ሴፕቴምበር ፪ ቀን ፪፻፲፬ ያተመዉ ዜና ረዕስ ፤)*

- ኢትዮጵያዉያን ሆይ / በአዲሱ ዓመት ጆሮአችሁንና ዐይኖቻችሁን ቀስራችሁ ወደ ደቡብ ምሥራቅ ተመልከቱ/...ሰሜነኛዉን ህልማችሁ ግና ሲያምራችሁ ይቅር ፤" እየተባልን ይሆንን ??? ...ወያኔ መቼም ኩምክና አያልቅበት ።

//

**"(በወያኔ ) የክፍያ መዝገብ ስማቸዉ የሰፈረ አሁን ድረስ ተቃዋሚዎች ነን እያሉ የሚንቀሳቀሱ የማዉቃቸዉ አሉ ። ....የነዚህን የማዉቃቸዉን ሰዎች ስም ላለመጥቀስ መርጫለሁ ።"**

*(የአረናዉ ወያኔ ገብሩ አሥራት በቅርቡ ባሳተመዉ "መጽሐፍ" ገጽ ፪፻፶፩ ላይ ያሰፈረዉና " ዘኢትዮጵያ" ጋዜጣ የዘገበዉ ፤)*

- የተሸጡትን ሰይጣኖች እያስፈራራህበት ይሆናል እንጂ ለአንባቢዎችህማ የነገርከዉ አንዳችም ቁምነገር የለም ። ይህችም ምስጢር ሆና መያዟ የሚገርም ነዉ ። " ወያኔ ለወያኔ ቢራገጥ ጥርስ አይሳበርም፤" የሚባለዉ እዉነት ኖሯል ።

//

**"ኢትዮጵያ ዉስጥ ጭቆናን ለማጥፋት የሞተ አንድም የለም ። ኢሕአፓም መኢሶንም የታገሉት / የሞቱት ለሥልጣን ነዉ ።"**

*"( ፕሮ / መስፍን ወ/ማርያም ከሸገር ኤፍ ኤም ሬድዮ ጋር በነሐሴ ወር ባደረጉት ቃለ መጠይቅ ያሰመሩበት መደምደሚያ ፤)*

- ዕዉቀትና ሸበት ቢያንስ ለዕዉነት ነቃሽነት ያበቃሉ የሚል ግምት ነበረን ፤ ግምቱ ግምት ሆኖ ቀረ እንጂ ። ....ሌላዉ ሁሉ ቢቀር ፤ ...ጭቆናን ሥልጣን ያልያዙ ወገኖች የትና እንደምን እንዳጠፉት አስረጅ ጠቅሰዉ ሊነግሩን በተገባ ። ረስተዉት ካልሆነ በቀር፤ ጭቆናን ፈንጠር ብሎ በሚጻፍ አቤቱታ መፋለም እንደማይቻልማ ራስዎ ከመንግሥቱ ኃ / ማርያም ያገኙት ተመክሮ አረጋግጦልዎት ነበር ።

ከገጽ 1 የዞረ

## ወያኔ ፤በዲሲ ኢትዮጵያዊያኖች እየተናጠ ነው

ከተለያዩ የሕዝብ ክፍሎች እና የፖለቲካ ድርጅቶች የተውጣጣው የዋሽንግተን ዲሲ ግብረ-ሀይል ባሳለፍነው 30 ቀናት ፤ ወያኔን የሚያቆስል እንቅስቃሴ ሲያካሂድ ከርሟል፡፡ የዛሬ ወር የጋምቤላ እና የውጋዴዎችን የጅምላ ጭፍጨፋ በመቃወም በአሜሪካ ውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት ደጃፍ ደምጹን ሲያሰማ የዋለውን ኢትዮጵያዊ ካሰናበቱ በኋላ የቆረጡ የግብረ ሀይሉ አባላት ወደ ወያኔ ኢምባሲ በማምራት ያን የግፈኞች ጎራ ለ 15 ደቂቃ በመቆጣጠር ያለ ሕዝብ ፈቃድ የተለጠፈበትና የኢትዮጵያን ሕዝብ የማይወክለውን የወያኔ ባንዲራ አውርደው በመጣል ልጥፍና ስርዝ የሌለበትን የኢትዮጵያ አረንጓዴ ቢጫ ቀይ በማውለብለብ ድንቅ ሥራ ሰርቷል፡፡ የነግርማ ብሩ አለቃ ሰለሞን ወዲ ወያኔ የተባለ የግቢው ተቀያሪ በፍርሀት ብዛት መሣሪያ በማውጣት ጀግኖች ላይ ቢተኩስም ፍርሀቱ ያለቀቀው በመሆኑ እንዲሁም በፈሪ እገዛ አንዳችም ጉዳት ሳያደርስ ቀርቷል፡፡ በማግስቱ ተጠፍሮ ወደ እትዮጵያ ተግዟል፡፡

ይህ በኢንዲህ እንዳለ በወያኔ በጀት ተጭነው የመጡ ወያኔዎች ወያኔን ድጋፍ በአሜሪካ ውጪ ጉዳይ ጽ/ቤት በሳምንቱ ሰልፍ የወጡ ቢሆንም በአጭር ጥሪ በመቶ የሚቆጠሩ ጸረ ወያኔ ሰልፈኞች በጎን በመሰለፍ ጉሮ ወሸባዬ ዘፍነውባቸዋል፡፡ ወያኔዎቹም ጭራቸውን ቆልፈው ሰልፉን ትተው ተበታትነዋል፡፡ የአቶ አንዳርጋቸውንም ከየመን መፈታትን በእንግሊዝ ኤምባሲ በየለኛ ለኛ ጠዋት የሚደረግ ሰልፍም ሳይተጓጎል እንደ ቀጠለ ይገኛል፡፡

የጋራ ግብረ ሀይል የወያኔን ተገዢዎች ማሳደዱን በመቀጠል ሐሙስ እለት በ 23 2014 የወያኔ ከንቲባ የሆነው ድሪባ ኩማና ካቢኔው ከዲሲ ከንቲባ ጋር ለመወያየት በተቀመጡበት ጽ/ቤት ደርሶ 5ኛ ፎቅ ቁጥር 507 በርግዶ በመግባት ወያኔዎቹን አሥሮ ለፖሊስ ለማስረከብ ከፍተኛ ትንቅንቅ አድርጎ የወያኔ ጉጅሌዎችን መግቢያ ቀዳዳ አሳጥተዋቸው ውለዋል፡፡

የጋራ ግብረ ሀይሉ እና የዋሽንግተን ፈርስት ሂጅራ በአንድነት አርብ በ 24 2014 ከኋይት ሀውስ እስከ አሜሪካ ውጭ ጉዳይ ጽ/ቤት ድረስ በጣም ድንቅ ሰላማዊ ሰልፍ አካሂደዋል፡፡




የኖርዎይ ኢሕአፓ የወጣት፣የሴቶች ክንፍ እና ደጋፊዎች በስዊድን የሚገኘዉን የወያኔን ኢምባሲ ለሰዓቶች ይዘዉት



የወያኔ ኢምባሲ ዘብኛ ተብየዉ ሰልፈኞቹ ላይ ሹጉጡን ሲያነጣጥር


Rose Unisex Hair Salon (Tsegereda)
6222 Georgia Ave. NW Washington, DC. 20011



የሴቶችንና የወንዶችን፣ የልጆችንና የአዋቂዎችን ፀጉር እናስተካክላልን። ለቀለም ፣ለሹርባ፣ ለፀጉር ስፌትና ለፐርም ሰራ ባለሙያ ከፈለጉ Rose Unisex Hair Salon





ከኢሕኣፓ ጋር ለሚደረጉ ግንኙነቶች የሚከተሉትን መጠቀም የቻላል

ስልክ፡ (202) 291-4217
ኢሜል፡ espic@aol.com
ፖስታ፡ EPRP
P.O. Box 73337
Washington, DC. 20056
ድረ ገጽ፡ eprp.com

ፍኖተ ዴሞክራሲን ለማዳመጥ Finote.org

ከኢሕኣፓ ወክንድ (EPRPYL) ጋር ለሚደረጉ ግንኙነቶች የሚከተሉትን መጠቀም የቻላል

ስልክ፡ (202) 291-5832
ኢሜል፡ eprpylnew@gmail.com
ፖስታ፡ EPRPYL
5309 Georgia ave.
Washington, DC. 20011
ድረ ገጽ፡ eprpyl.com

ካለፈዉ የቀተለ

## በቀይ ሽብር የሞት ጥላ ሥር ፤ የጓድ ቆንጂት ተክሉ ክራሞት

### ፬

ገዳዮቹ " አብዮት ጥበቃዎች" ፤ ከእያንዳንዱ ቀበሌ ጋር በመዋቅር ተያይዘዉ በ"ቀይ ሽብር ግንባር" ስር ይሰለፋሉ ። የሁሉም የበላይ የ "ቀይ ሽብር ኮሚቴ" ሲሆን ተግባሮቻቸዉንና " ሥርዓተ አልበኞችን" በመመንጠር ረገድ የሚያሳዩትን የቁርጠኛነት ስሜት ይቆጣጠራል ። የቀይ ሽብር ኮሚቴ ፤ የደርግ አባል - ለገሰ አስፋዉን በመሳሰሉ ሰዉ በላ ፋሺስቶች የሚመራ ሲሆን አባላቱ ደግሞ በቀበሌዎችና በማህበራት መዋቅሮች ዉስጥ ሰርገዉ የገቡ ዴሞክራሲያዊ አቋም ያላቸዉን ወገኖች በማስወገድ ስልጣናቸዉን በቁጥጥር ስር እስከማዋል ድረስ ሙሉ ሥልጣን የተሰጣቸዉ ነበሩ ። ከሰይጣናዊ ፈቃዶቻቸዉና ግምኛ ግብሮቻቸዉ በመነጨም ፤ በጊዜዉ በከተማይቱ ዉስጥ ፍጹም የገለማና ለስሜት የሚሰቀጥጥ ድባብ ሰፍኖ ቆዬ ።

በታህሳስ ወር የመጀመሪያ ሳምንት አካባቢ በማዴቦ ከሚሰማሩት ተሽከርካሪዎች ሁለቱ ወደ መርካቶዉ የአንዋር መስጊድ ቅጽር ዘልቀዉ በመግባት ፴ (ሠላሳ ) የሚደርሱ ፤ ከከፋ ክ/ሀገር የመጡ ሙስሊም ተሳላሚዎችን ጨፍጭፈዉ ገደሉ ። ከጥቂት ቀናት በኋላ ፤ በአገዛዙ ቁጥጥር ስር የነበሩት መገናኛ ብዙሀን ጭፍጨፋዉን " የኃይማኖት ልዩነትን ተንተርሰዉ ጥፋት ለማቀጣጠል ያቀዱ ሥርዓተ አልበኞች" ድርጊት አድርገዉ ለማቅረብ ያልተሳካ ጥረት አደረጉ ።

በዚያን ሰሞን ፤ በመቶዎች የሚቆጠሩ ወጣቶች ፤ ሠራተኞች ፤ተማሪዎች ፤ መምሕራን ፤ ምሁራንና የመንግሥት ሠራተኞች ከየመኖሪያ ቤታቸዉና ከየሚሠሩበት ሥፍራ እየተለቀሙ የተያዙ ሲሆን ፤ ከዚያ በኋላም ዳግመኛ በአካል አልታዩም ። ተመልካቹን ሕዝብ ለማሸበር ሲባል ፤ ተጠርጣሪ "ሥርዓተ አልበኞች"ን በተጨናነቁ አካባቢዎች ፤ ሰዉ በብዛት የሚተረማመስበትን ሰዓት መርጦ መረሸን ሥራ ተደርጎ ተይዞ ነበር ። የፍጅት ግብራቸዉንም ፤ " አካሉ የተሸነታተፈ አንድ ሬሳ ያን ያህል ሰዉን ለማሸበርና በፍርሃት ለማስደንበር ከቻለ ..... ለምን በመቶዎች አናባዛዉም ???...." በሚል የጨካኞች ፈሊጥ አስደግፈዉ የተሠማሩበት ይመስላል ። በታላቅ ዐረመኔያዊ ፍላጎት ተዉጠዉ ፤ ገላቸዉ የተከታተፈ አስከሬኖችን አነባብረዉ ጎዳናዎች ላይ ከመሩ ፤ በመገንጠያ መንገዶች ፤ በአደባባዮች ፤ በድልድዮች ላይ ለዕይታ ደረደሯቸዉ ። በዚህ መልኩ ፤ " ለጥ ሰጥ ብለህ ተገዛ ....አለበለዚያ ግን...."፤ የሚለዉ የፋሺስታዊዉ አገዛዝ ሞትን ያዘለ መልዕክት በቁም ወደአሉቱ ዜጎች በመተላለፍ ላይ ነበር ።

ቅጥረኞቹ ነፍሰ በላዎች ፤ ሬሣዎቹን ለሕዝብ ዕይታ ወደ አዉራ መንገዶች ከመወርወራቸዉ በፊት ይጫወቱባቸዉ ነበር ። አንዳንዶቹ አስከሬኖች ራሳቸዉ የተቆረጠ ፤ ከፊሎቹ እጆቻቸዉና እግሮቻቸዉ እየተጎነደሉ በግንባሮቻቸዉ ላይ በሚስማር የተመቱባቸዉ ነበሩ ። ጥቂቶቹ ደግሞ በደረቶቻቸዉ ላይ በሚስማር የተመታ " ጸረ - አብዮተኛ ነበርኩ" የሚል መፈክር እንዲነበብ ተደርገዋል ። የከተማ ነዋሪዎች ማኅበራት (ከነማ ) ተመራጭ የአመራር አባላት የነበሩ ጥንድ ባልና ሚስት ከተገደሉ በኋላ ፊታዉራሪ ኃብተ ጊዮርጊስ ድልድይ ላይ የተጣሉ ሲሆን ገዳዮቻቸዉ አንድ የዉስኪ ጠርሙስ ፤ ሦስት ብርጭቆዎችና የአጼ ኃይለ ሥላሴ የትዳር ጓደኛ የነበሩት የእቴጌ መነን የፎቶ ምስል እንዲዳበሷቸዉ አድርገዋል ።

የጥንዶቹ ሰለባዎች በድን ገላም ፤ በሀምራዊ ቀለም በተጻፈ አስበርጋጊ የቀይ ሽብር ፖስተር " አጊጧል" ። ከፒያሳዉ የአዉጉስታ ሽሚዝ መሸጫ መደብር መተላለፊያ ሠርጥ ላይ አንዲት ወጣት ሴትና አንድ ወጣት ወንድ በደረታቸዉ ወድቀዋል ። ደማቁ ቀይ ደማቸዉ ፤ ከአረንጓዴያማዉ ቢጫ ግድግዳ ላይ በርከት ብሎ ተረጭቶበታል ። የሥጋቸዉ ቅንጥብጣቢዎች ከደንጊያና ከስሚንቶ የተሠራዉን ስንጥቅጥቅ ግድግዳ መርገዉታል ። እጅግ ከቀረበ ርቀት ተኩሰዉ እንደገደሏቸዉ በግልጽ ይታያል ። በዚያዉ ግድግዳ ላይ ፤ ከደማቸዉ እየተጠቀሰ በጉልድፍ የእጅ ጽሁፍ የተጻፈ ለማመን የሚከብድ ወለፈንዲ ይነበባል።

## ትናንትና

... "ከነዚህ ሥርዓተ አልበኞች ለፈሰሰዉ ደም ተጠያቂዉ ዴሞ ነዉ /" የሚል ። ነፍሰ በላዎቹ የሚከተሉት አንዳች አስፈሪ ስነ አመክንዮ ኖሯቸዉ ኖሯል ። ..."ሰለባችን ሆነህ ከእጃችን ለመዉደቅህ ተጠያቂዉ የገዛ ራስህ ነህ ፤" የሚል። ከዋዛ የለሹ አመክንዮ የሚመዘዝ አንዳች ቀልድ ቢኖር፤ ድቅድቅ ጽልመትና ዳፍንት የጋረደዉ ከመሆን አያልፍም።

ፒያሳ እምብርት ላይ የተጣለዉ የአስከሬን ቁልል ፤ የሰዉ ሥጋ ክምርና የሰዉ ደም ኩሬ ማለቱ ይቀላል ፤በአብዮት ጥበቃዎች ለበርካታ ሰዓታት ሲጠበቅ ቆዬ ። የጥበቃቸዉ ምክንያቱ ፤ አስከሬኖቹ በገዛ ራሳቸዉ ከወደቁበት ተነስተዉ ይሠወራሉ ወይም ሌላዉ አንስቶ ይቀብራቸዋል ከሚል ፍርሃት የተነሳ እንዳልሆነ ግልጽ ነበር ። ይልቁኑ ተመልካቾችን ለመፈተን ፤- ማን እንዳዘነ ፤ የማንንስ ዐይኖች ዕንባ እንዳቋሩና ማን ከቁጥጥሩ ዉጭ ራሱን በሥርዓተ አልበኛነት ወይም በደጋፊነት እንዳጋለጠ ለመከታተል ሲባል የሚደረግ ነበር ። ያንን ሲያደርግ የተገኘ ሰዉ ደግሞ የእስራትና የእንግልት እጮኛ መሆን አይቀርለትም ። ሕዝቡ ግና አዩት ወይ አላዩት ደንታ አልነበረዉም ።አንድ ታዛቢ እንደተናገረዉ ፤ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ያለቅሱ የነበረ ሲሆን የተቀሩት ደግሞ ቁጣና ንዴታቸዉን ይገልጹ ነበር ። ከዚያ የከፋ ሁኔታ ሊኖር እንደማይችል በሚገባ አዉቀዉታል ። እኔዉ ራሴ በዕንባ በተጋረዱ ዐይኖቼ ፤ ወደ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በማምራት ላይ የነበሩ አንዲት ዕድሜያቸዉ የገፋ መነኩሲት ፤ ማን ምን ይለኛል ሳይሉ ፤ በዋይታ ደረታቸዉን እየመቱ ሙሾ ሲያወርዱ አይቻለሁ ። በዚያ የተጨናነቀ ጎዳና ላይ አዉቶቡስ ሲሳፈሩና ሲወርዱ የነበሩትም ፊታቸዉን በሃዘን ቅጭም ያደረጉ ሲሆን ከፊሎቹም አድራጎታቸዉ የሚያስከትለዉን ባለመፍራት ያለቅሱ ነበር ።

ከላይ የጠቀስኩትን የመሳሰሉ በመቶዎች የሚቆጠሩ ድርጊቶች በየዕለቱ ይፈጸሙ ነበር ። ሕዝቡ በድርጊቶቹ በርግጓልም ፤ ተቆጥቶማል ። በተቻለዉ አቅምም ለመቋቋም ሞክሯል ። ይህ ደግሞ በርግጥ እጅጉን ጠቃሚ የሆነ ሁነት ነበር ። እናም ከማኅበረሰቡ የተለያዩ ክፍሎች የፈለቁ ወጣቶችና አረጋዉያን የራስ አገዝ የመከላከያ ኮሚቴዎችን ለማቋቋም ተጣመሩ ። በኮልፌ ፤በተክለ ኃይማኖት ፤ በጎፋ ሠፈር ፤ በጎላ ሚካኤል ፤ በጣሊያን ሠፈርና በሌሎቹም አካባቢዎች የተዋቀሩት " የኡኡታ ኮሚቴዎች"፤ " የምከታ እና የ ፀረ- ዐፈና ኮሚቴዎች" በምሳሌነት የሚጠቀሱ ናቸዉ ። በዚህ ሁኔታ የተደራጁት የየአካባቢዉ ነዋሪዎች፤ የአገዛዙን የሌሊት አሳሾች ለማገድና ዐረመኔዎቹ ነፍሰ ገዳዮች የሚጓጓዙባቸውን ተሽከርካሪዎች ለመግታት የሚያስችሉ መሠናክሎችን ከማዘጋጀታቸዉም በላይ የመንገድ ዳር መብራቶችን አምፑሎች ይሰብሩ ነበር ። በድቅድቅ ጨለማ የሚደረጉት የሴቶች ኡኡታና ዋይታ ፤ እንዲሁም መጥበሻዎችንና መቀቀያ የብረት ድስቶችን በመምታት የሚፈጠሩት ድምጾች ነፍሰ ገዳዮቹን ከማስደንበራቸዉም በላይ ለተፈላጊዎቹ ሰለባዎች የማንቂያና የማስጠንቀቂያ ደወል ሆነዉ አገልግለዋል ። አንድ ምሽት ላይ ጎፋ ሠፈር ዉስጥ በተለመደዉ ተግባራቸዉ ላይ ተሰማርተዉ የነበሩ የአገዛዙ ነፍሰ ገዳዮች ፤ የአካባቢዉ የመከላከያ ኮሚቴዎች የወሰዷቸዉ መሰል ርምጃዎች ካሳደሩባቸዉ የጸና ፍርሐት የተነሳ ፤ የድጋፍ ጥሪ ያደረጉ ሲሆን ባለአዳኝ መብራት ሔሊኮፕተሮችና አነስተኛ ታንኮች በተደራቢነት ተሰልፈዉላቸዋል ።

በዚያዉ ዓመት የገና በዓል እየተቃረበ መምጣቱን ተከትሎ አሠሳው ፤ እገታዉና ፤ በአጠቃላይ ቀዩ ሽብር እየተጠናከረ ሄደ ። እግረኞችንና በመኪና ተጓጓዦችን ለመፈተሽ ሲባል እያንዳንዱን ጎዳና በደኅንነት ሠራተኞች ከሚገባዉ በላይ ማጨናነቅ የተለምዶ ሆነ ። ከአሠሳዎቹ የድግግሞሽ መጠን ፤ እንዲሁም ከሚታገቱት ፤ ከሚፈተሹትና በቁጥጥር ሥር ከሚዉሉት ሰዎች ቁጥር በመነሳት ወታደራዊዉ መስተዳድር ከጠቅላላዉ ህዝብ ዘጠና በመቶዉ " ሥርዓተ አልበኛ" (ኢሕአፓ) ሆኗል ብሎ ያምናል ከሚል ድምዳሜ መድረስ ይቻላል ። ቀበሌዎችና ከፍተኛዎች አዳዲስና ይበልጥ የተራቀቁ ጠመንጃዎች እንዲታጠቁ ተደርገዋል። ከ ኢ.አ 9501 እስከ ኢ.አ 9525 ባሉት ቁጥሮች የሚጀምሩ መንግሥታዊ ሰሌዳዎችን (ታርጋዎች) የለጠፉና ቢጫ ቀለም የተቀቡ ቮልስዋገን ሽፍን የማመላለሻ መኪኖች ለእያንዳንዱ ከፍተኛ ታድለዋል ።

ጃንሜዳ በሚገኘዉ የስፖርት ማዘዉተርያ ሥፍራ ተከታታይ የሥልጠና ልምምዶች በመደረግ ላይ ናቸዉ ። ከእያንዳንዱ ቀበሌና ከተለያዩ ተቋማት በጥንቃቄ ተመርጠዉ በድጋፍ ደብዳቤ ከተላኩ ከስምንት እስከ አስር በሚደርሱ የጥበቃ አባላት ተዉጣጣጥቶ የተደራጀዉና በታማኝነቱ ሌሎቹን የሚያስንቀዉ የአብዮት ጥበቃ ቡድንም ልዩና አፋጣኝ ኮርስ መከታተል ጀምሯል ። ይህ ለወደፊቱ በአስነዋሪ ግብሮቹ ስሙ የሚጠራ ግብረ ኃይል ልዩ ለሆነ ግዳጅ ብቃት እንዲኖረዉ በመሠልጠን ላይ ነበር ።

**ይቀጥላል........**

# ነጻ ሀሳብ

## መልኩ የእኒ፤ ግብሩ የአረመኔ

*ከየፍኖተ ዴሞክራሲ የተወሰደ*

ደርግንም ወያኒንም_ኢትዮጵያዊ ካላልን ብለው ሙግት የሚገቡ በጣም ያሳዝናሉ ። የደርግም የወያኒም አረመኒ አፈአዞች የኢትዮጵያ መንግስት ሊባሉ የሚችሉ አልነበሩም፤አይደሉምም። መውለድ ቋንቋ ነው የተባለውን ያስታውሷል፤ መልኩ የእኔ ግብሩ የአረመኔም መባሉን አንርሳ ። መንግስቱንም ሆነ መለስን በመልክ ቁርጥ የሚመስል ኢትዮጵያውያን የሉም ብሎ መከራከር ቢቻልም ውልደታቸው ኢትዮጵያዊ ቢሆንም (መለስ እንኳን ኢትዮጵያዊ ሳይሆን ከሆነ ወርቅ ዚጋ ተወለድኩ ባይ ነበር)ግብራቸው ግን የአረመኒ ነበር፤ነውም። በዚህም ኢትዮጵያዊነታቸው ይሻራል--ጻረ ሕዝብና ጻረ ኢትዮጵያ የሚባሉ ናቸውና ።ወያኔን የኢትዮጵያ መንግስት ማለትና ሚቹን አረመኒ አክብሮ አንቱ ማለት ተራ አጎብጓቢነትና ስህተት ነው ።

ታሪክ ሊሰረዝ አይቻልምና ከዛሬ 30ዎች ዓመታት በፊት ደርግ የተባለው የርኩስ መኮንኖች ቡድን በመስከረም ሁለት በኢሕ አፓ ላይ መሉ ጦርነትን አወጀ ። ይህን ያደረገበት ምክንያት ኢሕ አፓ ቀድሞ ጦርነት ስላወጀበት ሳይሆን ደርግና አጋሮቹ በፖለቲካው መስከ ሽንፈትን ስለደረሰባቸውና በዚህ ትግል መቀጠሉ አያዋጣንም ብለው ስለወሰኑ ነበር ። በሚያውቁትና በሰለጠኑበት ግድያ ተሰማሩ ።

ከ1967 ዓ፣ም ጀምሮ ደርግ ግድያና አፈና ሲያካሂድ መቆየቱን በዝርዝር ቀይ ሽብር በኢትዮጵያ በሚለው መጽሃፍ ላይ የሰመረ ሀቅ ነው ። አሁን የሚፈለገው የዲምክራሲ መብት ሳይሆን የዲሞትፎር ጥይት ነው ሲሉ የደርግ አጋሮችም አጓሩ። ከዚህ ቀጥሎ ለትውስታ (እንጥቀስ--ገጽ 75-79)

" የ 1969 ዓ.ም. የዘመን መለወጫ ከሚለው ጀምረህ እስከ ገጽ 80 መጨረሻ አንበው--የደብተራው ፎቶ ያለበት እትም ነው። የመስከረም 2 ትዝታችን እንደ ግንቦቱ 20 መራራና ደም የሚያፈላ ነው ። የሄደው የወደቀው ግፍ ዛሬ በወንጀለኞቹ ሊደበቅ ሲሞከር አረመኒዎቹ ታሪክ ይቀለብሱ ዘንድ ተፈቅዶላቸው መጽሃፍ አቅራቢ ሆነው ይወራጫሉ ። ደረቁ ሬሳ ትኩሱን አስረሳ ወደሚለው ሳንገባ ያለፈውን ግፍና ታሪክ መሳት ደግሞ ነፍሰ ገዳዮችን ማቀፍን ስለሚያስከትል ጠንቀቅ ይቅደም ለማለትም ነው ። መባሉንም ግድ የሚለው ስንቶቹ ሳይገደዱ ተጃጅለው መለስ ሞተ ብለው--ሰርጉን ተዝካር አስመስለው-ሲላቀሱና ርባና ቢስ እምባ ሲራጩ ማየታችን ነው ። ጉዳዩ ኢትዮጵያዊው ማነው፤ኢትዮጵያዊነትስ ምን ማለት ነውን ይጠቀልላል ወይም ይጠቅሳል ። ሀገሬ ሀገሬ ያለውና ራሱን በሰንደቅ አላማ የጠቀለለው ሁሉ ኢትዮጵያዊ ነው፤ሀገር ወዳድ ነው ሊባል አይቻልም ። ቢሆንማ ኖሮ ኢትዮጵያ ሀገሬ ብለው ያቅራሩት ሁሉ የወያኔ ቡችሎች ባልሆኑ ነበር ። ኢትዮጵያዊነት መጥቆር ወይም መጠየም ማለት አይደለም። በአሁኑ ተጨባጭ ሁኔታ ኢትዮጵያዊነት ፍጹም ጻረ ወያኔነትንና በኢትዮጵያ አንድነት ማመንን ይጠይቃል ። ኢዲሞክራሲያዊነትና ኢትዮጵያዊነትም ተጻራሪ መሆን አለባቸው/ናቸውም ። ለደርግ ያደሩና ዛሬም ለወያኔ ያደሩት ሁሉ ራሳቸውን ኢትዮጵያዊ ካሉ የሚያታልሉት ራሳቸውን ነው ። መወለድ ቋንቋ ነው ። ህግርም=ን መውደድ፤ለህገርና ለሕዝብ ህይወትንለመሰዋት ዝግጁ መሆንን ጥያቂ ነው ኢትዮጵያዊነት። ይህ ባልሆነበት ግን መልኩ የኢትዮጵያ ግብሩ ጻረ ኢትዮጵያ ብለን መደምደም የግድ ይሆናል ። ህገርና ህዝብ የተያያዙ ናቸው፤ከአረመኒ ጻረ ህዝብ ጫማ ስር ወድቆ ህዝብን መውደድ ሀገርን ማፍቀር ዘበት ነው ።'"

## ብሄራዊ ችግር ያለ ሁሉም ትብብር አይወገድም

*ከየፍኖተ ዴሞክራሲ የተወሰደ*

የሀገራችን የኢትዮጵያ ችግሮች ስፍር ቁጥራቸው የተትረፈረፈ ከሆነ ዓመታት አልፈዋል። እስካሁንም ፤ እነኝህ ችግሮች፤ ሊወገዱ ቀርቶ ሊቀረፈቱ እንኳን አልተቻሉም ። እንዲያውም፤ በአመዛኙ፤ ችግሮቹንም እንኳን ፤ መጠናቸውንና ጥልቀታቸውንም ቢሆን በሚገባ መረዳት መቻሉንም የሚጠራጠሩ ብዙ ናቸው ። ችግሮቹን በሚገባ መረዳት ካልተቻለ ደግሞ፤ መፍተሄውን አግኝቶ በሽታውን ማስወገድ ያስቸግራል ። ይህ በሚሆንበት ጊዜ ደግሞ፤ የችግሩን መፍተሄ ይፈልጋሉ ተብለው የሚጠበቁት ተቃዋሚ ድርጅቶች፤ ተባብረው ለመቆም አይችሉም ። መተባበር እንዳለባቸው ባለመረዳታቸው ምክንያትም፤ እስካሁን ድረስ የተቃውሞውን ትግል በሚገባ ሊመሩት አልቻሉም። ይህም ሊሆን የቻለው፤ በሚያስተባብራቸው የጋራ ጉዳይ ላይ መስማማት ስለአልቻሉ ነው። በዚህ ምክንያት ፤ የተጠበቀው ኅብረትና ትበብር ይመጣል ብሎ ለማመን አስቸግሯል ። ይህ በመሆኑም፤ የትግል እንቅስቃሴ እናደርጋለን የሚሉ በርካታ ድርጅቶች መልኅቅ እንደሌለው መርከብ አቅጣጫ- ቢስ ሆነዋል ማለት ይቻላል። በዚህ ምክንያት ሀገራቸውና ሕዝባቸውን ለወያኔ ሰለባ ዳርገዋቸዋል ። ከአዞ እምባ ይልቅ የደም መሥዋዕት መቅደም እንዳለበት ማንም የተረዳው የለም ።

ነጻነትን የመሰለ ጸጋና በረከት፤ ማንም በሌማት እንካ ብሎ የሚሰጥ የለም ። በመሆኑም፤ ለነጻነት መሥዋዕት መክፈል ግድ ነው። ታዲያ፤ ከጋራ ግንዛቤ በመነሳት፤ የጋራ ዕምነትና መተማመን እስከሌለ ድረስ፤ ኅብረትና ትብብር የሚባለው ጉዳይ የበረሃ ንብልብሊት ( ሚራዥ ) ሆኖ ይቀራል ። የምድረበዳ ንብልብሊት ([ሚራዥ ) የሚጨበጥና የሚዳሰስ እንደማይሆን ሁሉ፤ የሀገራችን መፍትሄ ፍለጋም የማይጨበጥ የማይዳሰስ ከሆነ ውሎ አድሯል ። ይህን አባባል ዕውን የሚያደርገው፤ ላለፉት ሃያ ሦስት ዓመታት የተካሄዱት የኅብረት ሙከራዎች ሁሉ ሙሉ በሙሉ ፍሬያማ አለመሆናቸው ነው። ይህን ማስረጃ ሊያስተበብል የሚችል ማንም የለም። ቢሆንም፤ ለትብብሩ ጥረት ፍለጋ የተለየዩ ኅብረተሰብ ክፍሎች ጥረት ማድረጋቸውን ግን ማስታወስ ይገባል። " ተባበሩ ወይም፤ ተሰባበሩ " የሚለው የቅሬታ መግለጫ የተቋጠረውም በዚህ ምክንያት እንደሆነ ይነገራል።

ላለመተባበር ቀንደኛ ምክንያቶች ከሆኑት አንዱ ፤ ሀገሪቱን የሚገዟት ጎሰኛ ግለስቦችና ስብስቦች ዕውነተኛ ምንነት በትክክል ያለማውቅ ችግር መሆኑን አምኖ መቀበል ያስፈልጋል ። ወያኔ፤ እስካሁን ሀገሪቱን ለማጥፋት ከፈጸማቸው ድርጊቶች በመነሳት ብቻ ፤ ስለ ወያኔ ማንነት፤ የሚሰጠው የደፈና ትርጉምና አገላለጽ የግለሰቦችን ስብዕና፤ አካሄድ ፤ ዓላማና ባኅርይ፤ በትክክል የሚገልጸው አይሆንም። ለመግለፅ ቢሞከርም፤ የተሟላ ሊሆን አይችልም ። ግለስቦችና ስብስቦች የሚጫወቱት ሚና እየተናቀ፤ በአመዛኙ፤ " በብዙሃን ታሪክ ሰሪነት " ላይ ማተኮሩ ብቻ አዘናጊና አሳሳች እንደሚሆን ከተመክሮ መማር ተችሏል ። በግለሰብ ደረጃ፤ የወያኔው ቆንጮ የነበረውን ሀገር-አጥፊ ግለሰብና የደርጉን ነፈሰ-ገዳይ ኮሎኔል ማስታወሱ ብቻ ይበቃል ። ሀገር-አጥፊ ግለሰቦች ሕዝብንና ሀገርን ከማውደማቸው በፊት መጥፋት ነበረባቸው። ያ ባለመሆኑ ሀገር አጥፍተው እራሳቸው እስኪጠፉ ድረስ በቂ ጊዜ ተሰጣቸው። ዛሬም ቢሆን፤ ሀገራችንንና ሕዝባችንን በማጥፋት ላይ ያሉትን ግለሰቦችና ቡድኖች ማስወገድ አልተቻለም። እነርሱ ጠፍተው እስኪጠፉ ደረስ፤ ሀገሪቱን እንደሚያጠፏት መታወቅ አለበት ። ነበረበትም ! በዚህ አንገብጋቢ ምክንያት ብቻ ተቃዋሚ ድርጅቶች መተበበር እንዳለበቸው ሊረዱት ይገባል ። ያ ካልሆነ፤ ሀገር ማዳናቸው ቀርቶ፤ እነርሱም ራሳቸው የሚጠፉበት ጊዜ እሩቅ አይሆንም። በተለያዩ የታሪክ አጋጣሚዎች እንደተከሰተው ሁሉ፤ ከባኅላዊ ግንዛቤና ከታሪክ ተመክሮ ብቻ በመነሳት፤ የጅምላ አገላለፅ መስጠት አሳሳች ነው። እስካሁን ድረስ የወያኔን ስብስቦች ባኅርይ፤ በትክክል ካለመረዳት የተነሳ፤ ሁሉ ነገር በግዴለሽነት ታልፏል። የትም አይደርሱም በሚል ንዝኅላልነትና ንቀት ብዙ መዘናጋት ተፈጽሟል። " ናቂ ወዳቂ ነውና " በንቀት እየታለፉ፤ የልባቸውን ከማድረግ የሚያግዳቸው አላጋጠማቸውም። ይህ በመሆኑ፤ የነርሱ በዕድሜ መሰንበት፤ ከደርግ ጋር ሲነጻጸር፤ ከሞላ -ጎደል አንጻራዊ "ሠላም " ና "ዕፎይታ" ሳያገኙ አልቀሩም ። ይህም በበኩሉ የልብ-ልብ ሰጥቶናል ብለው እራሳቸውን እስከመደለል አብቅቷቸዋል ለማለት የሚቻል ይሆናል።

ወያኔዎች፤ ከድንቁርና ትዕቢት በመነሳት የራሳቸውን ጉልበትና አቅም ከሚገባው በላይ በመለጠጣቸው፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ ኃይል አሳንሰው እስከማየት ደርሰዋል። ይህም በሌላ ረገድ ሲታይ፤ በተቃዋሚው ጎራ ነን የሚሉ ድርጅቶች፤ የወያኔን ጉልበትና ኃይል በሚገባ ተንትነው በማወቅ የትግል ታክቲክና ስታራተጅ ነድፈው የጋራ ትግል ለማካሄድ አልተቻላቸውም ። ይክ እስካልሆነ ደርስ ደግሞ ወያኔን ማንበርከክ ዘበት ነው።

በመሠረታዊ ባኅርዩና ድርጊቱ፤ የአምባገነን ሥርዐት አራማጆች፤ ለሥልጣናቸው የሚኖራቸው ቀናዒነት ተመሳሳይነት አለው ለማለት ቢቻልም፤ በሀገር አሳቢነት ደረጃ፤ ደርግንና ወያኔን በአንድ ሚዛን ማስቀመጥ ይከብዳል የሚሉ የፖለቲካተንታኞች በርካታ እንደሚሆኑ ይገመታል። በግለሰብ ሚና አፋረጃጀትም ከሆነ፤ የደርግ አባላትን እንደ ሀረግ እሬሳ አሽመድምዶና አኮላሽቶ ሁሉን አራጊ -ፈጣሪ በመሆን ሕዝብ ጨርሶ ከሀገር በኮበለለው ግለስብ ኮሎኔልና ፤ በብሄር ድርጅት የተሰባሰበውን የወያኔንና የጋሻ ጃግሬዎቹን ጥርቅምቃሞ እንደ አሻንጉሊት ኅልቶ በጠፋው የወያኔ መሪ መካከል ልዩነቱ እምብዛም ነው ። በደርግ " ኢትዮጵያ ትቅደም " መፈክርና "ጀርመን መጀመሪያ ! " በሚለው የሂትለር ሠላምታ አሰጣጥ መካከል ብዙም የጎላ ልዩነት እንደሌለው ሁሉ፤ ኢትዮጵያን በማጥፋት አኳያ በደርግና በወያኔ መካከል ያለው ልዩነትም እንደዚሁ፤ ይህን ያህልም ኅልቶ የሚታይ አይደለም ። አንድን ሃቅ ግን መካድ አይቻልም። ይኸውም፤ ወያኔ ዘረኛና ኅጠኛ በመሆኑ፤ የኢትዮጵያ እንደ ሀገር መኖር አለመኖር ደንታ የሚሰጠው አለመሆኑ ነው።

ለዚህም ነውወያኔ፤ የኢትዮጵያን ስም አጥልቆ ነገር ግን፤ ኢትዮጵያን እያጠፋ መቀጠሉን ብዙዎቹ ሊረዱት ያልተቻላቸው። " ጅብን ሲወጉ በአህያ ይጠጉ " በመሆኑ፤ ወያኔዎቹና ተባባሪዎቻቸው፤ የኢትዮጵያን ለምድ ለብሰው ኢትዮጵያን ቢያጠፉ አያስደንቅም ። የሚያስገርመውና የሚያንገበግበው ግን የእነርሱን ትክክለኛ ማንነት ሁሉም ተረድቶ፤ እነርሱን ለማስወገድ አለመተባበሩ ነው።

የተወስኑ ክፍሎች፤ ወያኔ፤ ኢትዮጵያን እያጠፋ መቀጠሉ ሊታያቸው ያልቻለው፤ ከራሳቸው የግል ጥቅም አኳያ ስለሚያዩት ነው እንጅ፤ ዕውነትስ የሀገሪቱን ጥፋት ሳይገነዘቡት ቀርተው አይደለም። የኢትዮጵያ ዕምነትና አመለካከት ኖሮት ሕዝቧን የጨረሰው ደርግና ኢትዮጵያዊነትን ሳይቀበል ኢትዮጵያን በሚያጠፋው ወያኔ መካከል ልዩነት የለውም እስካልተባለ ድረስ፤ ወያኔንና ደርግን በአንድ ሚዛንና መስፈርት አስገብቶ መገምገም፤ ከትክክለኛ ብያኔ ላይ አያደርስም። ጅብ ሆነ አዞ ሁሉም ቢበላኝ ባገጠጠ ጥርሱ ነው ማለቱ እንድተጠበቀ ሆኖ። ለዚህም ይመስላል፤ ወያኔን ተጻርረን ቆመናል የሚሉት ድርጅቶች፤ በዕርግጥም፤ የወያኔን ማንነት በሚገባ አልተረዱትም ተብለው የሚወቀሱት።የጋራ ጠላታቸው የሆነውን ወያኔን በሚገባ ተረድተውት ቢሆኑማ ኖሮ፤ እስከዛሬ ድረስ የጋራ ግንባር በመፍጠር ታግለው፤ ሀገራቸውንና ህዝባቸውን ከወያኔ አገዛዝ ቀንበር ነፃ ባወጡ ነበር ። ተጻርረው የሚታገሉትን ባላንጣ ዕውነተኛ ማንነት በዕርግጠኝነት እስካለረዱት ድረስ፤ ብርታቱንና ድክመቱን በሚገባ ሊያውቁት አይችሉም። ያ ከሆነ ደግሞ፤ ዒላማን ወደ ማን ላይ ማነጣጠር የሚቻል አይሆንም። ኢላማን መሳት ከመጣ ደግሞ፤ ትግል እናካሂዳለን የሚሉት ድርጅቶች ፤ የሚሄዱበት መንገድ ሁሉ የዳበሳ ጉዞ ሆኖ ይቀራል። መደናበር ከመጣ፤ መጠቃትን እንጅ ማጥቃትን አያስገኝም። እስካሁን የሆነው ይህ ክስተት ነው። ተባብሮ ለመታገል፤ በግድ የጋራ ዓላማና ግብ እንዲኖር ያስፈልጋል ። ያ ባለመኖሩ ነው እስካሁን በአንድ አቅጥጫ መጓዝ ያልተቻለው። የትግል ትብብር እንዲኖር ካስፈለገ፤ በቅድሚያ በሚከተሉት መሠረታዊ ጉዳዮች ላይ የጋራ ግንዛቤ እንዲኖር ግዴታ ነው።

- በኢትዮጵያ ሀገራዊ ሉዓላዊነት ማመን፤ ከሁሉም በፊት ቅድሚያ የሚሰጠው ይሆናል ።
- በሕዝቦቿ አንድነትና ዕኩልነት ላይ፤ ፈጽሞ መደራደር የማይቻል መሆኑን አምኖ መቀበል ግዴታ ነው።
- የሀገሪቱን የተፈጥሮ ሀብት ሁሉም ዜጋ በዕኩልነት የመጠቀም መብት እንዳለው ማወቅ ያስፈልጋል ።
- በዘርና ሃይማኖት ላይ የተመሠረተ ሥርዓተ-መንግሥት በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ማመን፤ የቅድመ -ትብብር ሀ ሁ ነው ።
- ከዚህ መሠረታዊ ዕምነት ተነስቶ ፤ ዛሬ በሀገሪቱ ላይ የተንሰራፋውን ዘረኛ ሥርዓት ለመለወጥ ተባብሮ መነሳት አማራጭ እንደሌለው ተረድቶ በኅብረት መታገል አማራጭ አይኖረውም ።
- ኢትዮጵያ፤ ምን ዓይነት ሥርዓተ- መንግሥት ሊኖራት እንደሚገባ ውሳኔው የዜግቿ ሙሉ ሥልጣንና መብት እንደሆነ ማወቅ የማነኛውም ደርጅት ግዴታ ሊሆን ይገባል

በእነኝህ አንኳር ኣንኳር በሆኑ ጉዳዮች የሚያምኑ ድርጅቶች ተስማምተው የትብብር መርሃ -ግብር መንደፍ የሚችሉ ከሆነ ፤ የጠራ አቅጣጫ ይዘው መታገል ይችላሉ ተብሎ ይገመታል ። ይህ ዕውን የሚሆን ከሆነ፤ ቢያንስ ቢያንስ፤ የወየኔን የክፍፍል ተንኮል በጋራ ለማክሸፍና ለመቋቋም ጥንካሬ ሊኖራቸው ይችላል ።

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

ከገጽ 6 የዞረ

ያንን ማድረግ ከቻሉ ፤ ከሞላ ጎደልም ቢሆን፤ የወያኔን ማንነት ተረድተዋል ማለት ይቻል ይሆናል። ይህም አዲስ ክስተት፤ አሁን በዘረኞች ይዞታ ስር ያለውን የፖለቲካ ምኅዳር ባቻ ሳይሆን ፤ ዛሬ ኢትዮጵያ የምትገዛበትን የዘረኞች ርዕዮተ- ዓለም ደምስሶ ፤ የሀገሪቱን የፖለቲካ፤ የኢኮኖሚ፤ የማኅበራዊና አስተዳደራዊ ምልከዐ- ምድር ( ላንድ ስኬፕ) መለወጡ አይቀርም። ያን ጊዜ፤ የኢትዮጵያ ብሩኅ ተስፋ፤ ብርሃን ይፈነጥቅበታል ። ይህን ተስፋ ለማየት በጉጉት የሚጠባበቀው ሕዝብ፤ ሁለንተናዊ ትብብር ለማድረግ ሆ ! ብሎ እንደሚነሳ ጥርጥር ሊኖር አይችልም ።

የተቃዋሚ ኀይሎች፤ ከላይ በተዘረዘሩት መሠረታዊ ጉዳዮች ላይ በመነሳት የጋራ ተግባራቸውን ማካሄድ ሲጀምሩ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚጠበቅበትን የራሱን ሀገራዊ ድርሻ እንደሚወጣ የታወቀ ነው ። አዲስ ሥርዓት ለማምጣት ሁሉንም ዜጋ ያሳተፈ ትግል የማካሄዱ አስፈላጊነት አጠያያቂ አይደለም። ከሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል ልዩ ልዩ ትብብሮችና ተሳትፎዎች ይጠበቃሉ ። እነኝህ ተሳትፎዎች ፤ የመረጃ መስብሰብንና ጥንቅርን ፤ የገንዘብና ቆሳቆስ ( ማቴርያል) ርዳታን ሁሉ ያጠቃልላል። የሀገሪቱ ምሁራን ሚና ወሳኝ መሆኑንም መገንዘብ ያስፈልጋል ። በተለይም ሀገር -ወዳድ ምሁርን የሚሳተፉበት ትግል ቦታ ሊኖረው ይገባል ። ሁሉንም የኅብረተ-ሰብ ክፍል ድጋፍና ተሳትፎን ያካተተ ትግል መምጣቱን ሲገነዘብ ፤ ወያኔ፤ ዕውነተኛ አቅሙ ምን ሊሆን እንደሚችል ስለሚገነዘብ፤ ሥልጣኑ አደጋ እንደሚገጥመው ሳይወድ በግድ ይቀበላል ።

ማነኛውም ሥርዓት፤ የሕዝብን ቁጣና የትግል ማዕበል መቋቋም ከማይችልበት ደረጃ ከደረሰ፤ ብል እንደበለው ማግ ተፍረክርኮ መበጣጠሱ አይቀርም። አምባገነን ይህንን ዕውነታ ተቀበለም አልተቀበለ፤ ሳይወድ በግድ፤ ለሕዝብ ይንበረከካል ። ወያኔም ከዚህ ሀቅ አያመልጥም። ይህ ከመሆኑ በፊት ግን፤ በመጨረሻው ሰዓት የሚወስዳቸው የኣልሞት ባይ-ተጋዳይ መፍጨርጨርና የነፍስ- አድን መፈራገጥ ሊያደርግ ይችላል ። ይህንን ሙከራ ለማድረግ የሚቃጣውም፤ ምናልባት ፤የጦሩ ኃይሉን ዕዝ እቆጣጠረዋለሁ፤ የጸጥታ መዋቅሩም ገና ከመዳፌ አልወጣም ፤ የፕሮፓጋንዳውንም መሳሪያዎችንም መጠቀም እችላለሁ የሚለው ተስፋው ገና ባለ መሟጠጡ ሊሆን ይችላል። " እኔ ከሌለሁ ሀገሪቱ ትፈርሳለች " የሚለውን የማታለያ ምክንያትም በመምዘዝ ሊቆምርም ይችል ይሆናል። የወያኔንና የኢሕአዴግን ስምና ቆዳ ለውጦም፤ " ሀገራዊ ፓርቲ " ሆኛለሁ ብሎ--ጀሊዎችም አሰልፎ-- ሊያታልልም ይችል ይሆናል ። እነኝህ አስተሳሰቦች ( ሎጅክ ) ግን ሊሰሩ አይችሉም ። ከዚህም በላይ አልፎ-ተርፎ ፤ እስከመጨረሻው እቋቋማለሁ የሚል ልብ አይኖረውም።

የወያኔ ከንቱ መብተክተክና ዋይታ፤ ከታሪክ ፍርድና ከኢትዮጵያ ሕዝብ ውሳኔ አያድነውም። በባዕዳን መተማመን፤ ዋጋ ቢስ ነው የሚሆነው። የደርግና የሶቭየት ኅብረትን ዝምድና ያጤኗል ! " በአህያ ቆዳ የተሰራ ቤት ይፍረከረካል ጅብ የጮኸ ዕለት" የሚለው ይትብብሃል እንደተጠበቅ ሆኖ፤ የተቃዋሚው ጎራ ኅብረቱን አስተባብሮ መታገል ታሪክ የጣለብት አደራ እንደሆነ መገንዘብ አለበት ። ለዚህ፤ ተግባር የመጀመሪያው ርምጃ የወያኔን ማንነት በሚገባ ማወቅ አስፈላጊ ነው ። የወያኔ በሥልጣን መሰንበት፤ በኢትዮጵያ ኅልውና ላይ ከፍተኛ አደጋ መሆኑ በይካድም፤ ኢትዮጵያ ሀገራችን ግን በዘለዓላማዊንቷ እንደምትኖር አንጠራጠርም

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር !!!!

ከገጽ 2 የዞረ

ብሎ ወደ ላይ የዘለቀው ማማ ለሕንጻው ተጨማሪ 100 ሜትር ከፍታ ሰጥቶታል፡፡ ሕንጻው አምስት ጋላሪዎች አሉት፡፡ በዕለቱ በክብር የተጋበዝነው 800 ሰዎች ስንሆን ለጉብኝቱ እንዲያመች በሰዓት ልዩነት ተከፋፍለን ቀዳሚዎቹ ወደ ውስጥ ዘው አልን፡፡ በመጀመሪያ የተቀበለን ይህ ክፍል (ጋላሪ ይሉታል) ሆን ተብሎ ብርሃን እንዲቸግረው ተደርጎ የተሰራ ነው፡፡ ፊለፊታችን ላይ ባለው ሰፊ ግድግዳ ላይ ጀርባቸውን የሰጡን የተቀመጡና የቆሙ ሰዎች ይጽፋሉ፡፡ "እንኩዋን ደህና መጡ" የሚለውን የኛን ሰላምታ በአማርኛ የሚጽፈው ሰው ጥላው ጎዘፍ ያለ ነው፡፡ እየቀረብን ስንሄድ የቆመም የተቀመጠም ሰው አላየንም፡፡ ተሳሳቅን፡፡ የዲጅታል ምትሃት ነው ላካስ፡፡ ቤተመዘክሩ በዲጂታል ጥበብ የዳበረ ነው፡፡ በዚህ ክፍል መሃል የነአሊ ምስል በፓስተር መልክ ቆሟል፡፡ በአሊ ፓስተር ላይ "ዝምታን መስበር" የሚል ጽሁፍ ቀይ ሽብር ምንነት ሊነገር የሚገባው ገድል ስለመሆኑ ለመመስከር ቀርቧል፡፡ እኛም ሌሎችም ጎብኝዎች ግርማ ሞገሱ ደመቅ ካለው ከአሊ ፎቶ ጎን ለማስታወሻ ፎቶ ወሰድን፡፡

ወደ እያንዳንዱ ጋለሪያ ወይ በኢሊቬተር አለያም በእግር መሄድ ይቻላል፡፡ የሚመረጠው ግን በእግር አቀበት እንደሚወጡ የተሰራውን የቻይና ግንብ መሰሉን መንገድ መያያዙን ነው፡፡ ደረጃ አይደለም፡፡ ደረጃ አልባ የሆነ ጠመዝማዛ አቀበት ነው፡፡ የኛ ቀይ ሽበር እይታ የሚቀርበው በጋላሪ አራት ውስጥ ነው፡፡ የአሊን የቀይ ሽብር ገለጻ ለማዳመጥና ፊልሙን ለመመልከት የዲጂታል ቅንብሩን መንካት ነው፡፡ የዘለሉት ነገር ካለ መመለስ ይቻላል፡፡ ፋሺስቱ መንግስቱ ሃይለማሪያም እንደ አበደ ውሻ እየተወራጨ የሰው ደም የሞላውን ሶስት ጠርሙሶች ተራ በተራ ከመሬት ሲያፈርጥ የሚያሳይ ፊልምም አለ፡፡ ለናሙና የቀረቡ የቀይ ሽብር ሰለባ የሆኑ ብርቅዬ የኢትዮጵያ ልጆች ፎቶዎችም ይታያሉ፡፡ ይህ ቤተመዘክር ዛሬ በህይወት ላሉት የግማሽ ሚሊዮን የቀይ ሽብር ሰለባ ቤተሰቦችና መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ታላቅ ታላቅ እጅግ ታላቅ የደስታና የድል ገድል አጎናጽፎናል፡፡

አምስተኛው ጋላርያ ሲደረስ የእግር መንገዱ ያልቃል፡፡ በህንጻው አናት ላይ ባለ አንድ መቶ ሜትር ማማ ተቀጥሏል፡፡ከፍታን የማይፈራ ሰው ደግሞ እስከጫፍ በኢሊቬተር ተጉዞ ከተማውን በሚገባ ማየት ይችላል በርግጥ ከተማውን ከጋለሪ 5 ላይም ሆኖ ማየትም ይቻላል፡፡ የቤተመዘክሩ ስራተኞች ቢሮ ለጎብኝዎች ወለል ብሎ ይታያል፡፡ በመስታውት ግድግዳ ውስጥ ናችው፡፡ ከውጭም ከውስጥም የሚሰሩትን ሁሉ ማየት ይቻላል፡፡ ግልጽነትን ለማሳየት ተብሎ የተነደፈ ነው ተብለናል፡፡ በነገራችን ላይ ከጋላሪ አንድ እስከ ጋላሪ አምስት ድረስ ርቀቱ አንድ ኪሎ ሜትር ነው፡፡ ይህን የቀይ ሽብር ታሪክ ወደ ቤተመዘክሩ ለማስግባት የሶስት አመት ድካም እንደፈጀበት አሊ ገልጾልኛል፡፡ የአሊ የግል ታሪኩ ለቀይ ሽብር ዝምታ መሰበር ምክንያት ነው፡፡ ማለትም ቀይ ሽብር በገሃድ ልክ እንደ ሆሊኮስት ሊዘከር በቅቷል፡፡ "የቀይ ሽብርን ታሪክ ለዚህ ድል ማብቃትህ ያስመሰግንሃል" ሲባል አሊ " "የሁላችንም የስራ ውጤት ነው፡፡" ብሎ ሙግት ይይዛል፡፡ በርግጥ የአሊ ታሪክ ከብዙዎቹ የቀይ ሽብር ተራፊዎች አንዱ ነው፣ የብዙዎች ታሪክ ነው፡፡ የግሉ የታሪኩ ስለቀይ ሽብር የሚለው ብዙ ነገር አለው፡፡ አሊ ከቀይ ሽብር ተራፊዎች አንዱ ነው፡፡ ህይወቱን ለብዙሃን የሰጠ ነው፡፡ ያንን ክፉ ዘመን አሳልፎ ዛሬ ምነው እንደነሱ ባደረገልኝ የሚያስብል ቤተሰብ ሰርቷል፡፡ ኑሮአቸው ሩጫ ነው፡፡ ረፍት የሌላቸው፡፡ ከግል ኑሮአቸው በላይ ለሌላው ይደክማሉ፡፡ "አሊ ይርባቸዋል፣ምሳ ውሰድላቸው፡፡" በማለት አይኔ ሆስፒታል ታመው ስለሚገኙት ሰው በመጨነቅ ለአሊ ትነግረዋለች፡፡ ያሞቀችላቸውን ምግብ አንስቶ "ተነሱ ሆስፒታሉ ሳይዘጋ እንድረስ" አለ አሊ፡፡ እኔም ተጨምሬ የታመሙትን አዛውንት ጠይቀን ተመለስን፡፡ መንፈሴ ረካ፡፡ለአሊ ይህ ሰሞን የደስታ ጊዜው ነው፣ ምክንያቱም ቀይ ሽብር ለበርካታ ሩጫ፡፡ በመሃል ወደ ስራው ሩጫ፡፡ ይህ ሰዎች ዕይታ ለቤተመዝክር በመብቃቱ፡፡ ካንዱ ሚዲያ ቃለ መጠይቅ ወደ ሌላው፡፡ ይህ ሰው ብዙ ነገር ነው፡፡ ገጣሚ ነው፡፡ ያውም ፈጣን ገጣሚ፡፡ አዝናኝ ነው፣ ቀልዱ የማይጠገብ፡፡ የልጅ ልጁ አንዲት ጋዜጠኛ ድንገተኛ ጥያቄ እንዲህ ስትል ጠየቀችው "ለመሆኑ ስለ አያትህ ምን ይሰማሃል?" እንዲህ አላት"ብዙ ሰው እንዲህ አይነቱን ስራ የሚሰራው ለገንዘብ ሲል ነው፣ አያቴ ግን መልካም ስራ የሚሰራው ለገንዘብ ብሎ አይደለም" ከልጅ ያልጠበቀቻቸው መልስ ነበር፡፡ በርግጥ ሶሴፐ በጀት የለውም፡፡ ሁሉም አባላቱ የሚያካሄዱት የሰብአዊ መብት ትግል የሚያንቀሳቅሱት ከቤተሰባቸው በጀት በመቀነስ ነው፡፡

ሶሴፐ በካናዳ ከፍተኛ ተደማጭነት አግኝቷል፡፡ ከዚህ ቀደም እንደዘገብኩት በአመት አንዴ " መዳረሻቸው ስለጠፋው የፓለቲካ እስረኞች" የምሽት ዝግጅት ሲኖረው ተሳታፊና ተባባሪ ድርጅቶች እንዲሁም ዝግጅቱን ለመመልከት የሚገኘው የስው ብዛት በርካታ ሲሆን በምሽቱ የሚቀርቡት ዝግጅቶች በሙሉ ቀስቃሽና አዝናኝ ናቸው፡፡ እንዲሁም "ለመብትህ ሩጥ" የሚለው የቀን ዝግጅት ቁጥራቸው በርካታ የሆኑ ሰዎችን የሚያሳትፍ ሩጫ ነው፡፡ ሯጮቹ በከነቴራቸው ላይ በእስር የሚማቅቁ የፓለቲካ እስረኞች የሚያስታውስና እንዲፈቱ የሚጠይቅ ነው፡፡ እነዚህ ዝግጅቶች ወደ ሰሜን አሜሪካ፣ አውሮፓና አሺያና መዝለቅ አለባቸው፡፡ የቀይ ሽብርን እልቂት ሳንታክት ማንሳትና ለሕዝብ ማሳወቅ አለብን፡፡ ስለ ቀይ ሽብር ታሪክ ስናነሳ ለብቀላ ሳይሆን ለማስተማሪያ መሆኑን መታወቅ እንዳለበት ተደጋግሞ መነገር አለበት፡፡ ተወደደም ተጠላ የቀይ ሽበር ሰለባዎቹ ጀግኖቹ የኢ ሕ አ ፓ አባላትና ለውጥ ፈላጊው ሕዝብ ነበር፡፡

ባንደኛው ጋላሪ ጥግ ሰወር ያለች ጠባብ ክፍል ውስጥ "እኔም ሕዝብ ሊሰማው የሚገባው የሰብአዊ መብት ጥሰት ተካሂዶብኛል፡፡ ታሪኩም እንዲህ ነው . . . " ብለው ታሪኮን ለተመልካችና ላዳማጭ ማቅረብ ይችላሉ፡ቅጅውን ሌላው ሊሰማውና ሊያየው ማድረግ ይችላሉ፡፡ በርግጥ ይህ ቤተመዘክር ያልዳሰሰው የሰብአዊ መብት ጥሰት ያለ አይመስለኝም፡፡ ቀይ ሽብር፣ ሆሎኮስት፣ ስለካናዳውያን አቦርጅናሎች ግፍ፣ ስለ ሴቶች መብት፣ ስለ ጌዮች መብት መረገጥ፣ ስለ ሕጻናት መብት፡ ስለ ሩዋንዳ ዘር ማጥፋት፣ ስለ መንግስት ስልጣን አለ አግባብ መጠቀም፣ ስለ ማንዴላ፣ ማህተመ ጋንዲ፣ የጥቁሮች ትግልና ማርቲን ሉተር ኪንግ ወዘተ ወዘተ ወዘተ ሁሉም ሕዝብ ወይም ጎብኝ በቀላሉ ሊረዳው እንዲችል ሆነው ቀርበዋል፡፡

የሙዚየሙን የሪሰርች ሃላፊ የሆኑትን ዶ/ር ጀርሚ ማሮንን የቀይ ሽብሩን ታሪክ ለማዳበር ተጨማሪ መረጃዎችን ማቅረብ መቻል አለመቻሉን ጠይቄያቸው በሚገባ እንደሚቻል ገልጸውልኛል፡፡ እንዲያው እኛስ የቀይ ሽብሩ ባለታሪኮች የሆነው ኢትዮጵያውያን የደስታችንን ምክንያት ብናውቀውም ቀይ ሽብር ታሪክ ለቤተመዘክሩ የሚኖረውን አስተዋጽዖ ምን ሊሆን እንደሚችልም ጠይቄያቸው ከሰጡኝ መልስ ውስጥ የሚከተሉት ነጥቦች ጎልተው ታይተውኛል፡፡ አንድኛ ቀይ ሽብር ለቆምንለት የሰብአዊ መብት መከበር አንዱ ክፍል ነው፡፡ ታሪኩ የሁሉም ዓልፎም የሕዝብ ታሪክ ነው፡፡ ሁለተኛ በርካታ ሰዎች ስለ ቀይ ሽብር እውቀቱ የላቸውም፡፡ በመሆኑም ሰዎች እንዲሰሙትና እንዲያውቁት ማድረግ አለብን፡፡ በርግጥም ቀይ ሽብር አላስፈላጊ የሰው ልጆች ጭፍጨፋ ነበር፡፡ ፍትህ፣ ዲሞክራሲንና ሰላምን ለጠየቀ ዜጋ የሚሰጥ ምላሽ መሆን አልነበረበትም፡፡

አሊ ሁለቱን የዊኒፔግ የሶሴፐ ዝግጅቶች ማለትም "መዳረሻቸው ስለጠፋ የፓለቲካ እስረኞች የምሽት ዝግጅትና ለመብትህ ሩጥ ዝግጅት ዝግጁ እንደሆኑ ነግሮኛል፡፡ የሰብአዊ መብቱን ትግል በጀርመን አገር ለማጠናከር በቅርቡ ልጁን ምሳሌን ይዞ ይሄዳል፡፡ ድንቅ ስራ እንደሚሰሩ ከወዲሁ መገመት ችያለሁ፡፡ ግሩም ቡና ካለው ካንድ የሶሴፐ ደጋፊ ቡና ቤት ጎራ አልን፡፡ ኮሮምቦላ የሚጫወቱ ወገኖቼን አስተዋልኩ፡፡ አዲስ አበባን አስታወሱኝ፡፡ ቡናችንን እየጠጣን ስልክ መጣበት፡፡ "ስለ ቀይ ሽብር ማብራሪያ እንድሰጥ ባንድ ታላቅ የምሽት ዝግጅት ግብዣ ተደርጎልኛል" አለኝ አሊ፡፡ ምን እንደሚላቸው ስለማውቅ ምን አልካቸው አላልኩትም፡፡ "ቀይ ሽብሩን በሚገባ አብራራለሁ፡፡ ዛሬ በወያኔ እስር የሚማቅቁ የፓለቲካ እስረኞች በሙሉ እንዲፈቱ ታዳሚው እንዲተባበረኝ እጠይቃለሁ፡፡ ወያኔ አፍኖ የት እንዳደረጋቸው ስለማይታወቁት ስለነ ጸጋዬ ደብተራ ስለነ አበራሽ ለታዳሚው አሳውቃለሁ" አለኝ፡፡ የቀይ ሽብር ታሪክ ለቤተመዘክር መብቃቱን ሰሞኑን ስናከብር ከረምን፡፡ ከፊቱ በርካታ እቅዶች ይጠብቁታል፡፡ የተጨናነቀውን ጊዜውን ገና ብዙ የሚያጨናንቁ ዝግጅቶች ተደርድረዋል፡፡

ተልዕኮዬ በሚገባ መሳካቱን በኩራትና በደስታ እያስታወስኩኝ ከዊኒፔግ አውሮፕላን ጣቢያ ደረስን፡፡ በሰላም ያግባህ ብሎ እኔም በቸር ያቆያችሁ ብዬ ተለያየን፡፡ የኢምግሬሺን ሃላፊዎች መጠየቅ ይወዳሉና አንዱ ወዴት እንደምሄድ ጠየቀኝ፡፡ ወደ ምሄድበት ቦታ ሊከለክለኝ መብት አልኩትና ከት ብሎ ሳቀ፡፡ በመጨረሻ እኔ ወደ በረራዬ እሱም ወደ ፍተሻው አቀና፡፡ የእንጀራ ጉዳይ ሆኖበት፣ሆኖብኝ፡፡

በቸር ይግጠመን! 09/26/14

# ዕውነትና ንጋት እያደር ይጠራል።

**እነ ፀጋዬ ደብተራው ለዘለዓለም ሕያው ኢትዮጵያዊ ሰማዕታት ናቸው በቅርቡ ኢሕአፓ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ወያኔ እነፀጋዬ ደብተራውን ስለመረሸኗ የወጣውን መግለጫ አስመልክቶ የአሲምባ አስተያየት**

ከጥቂት ቀናት በፊት ኢሕአፓ አንድ የድሮ ወያኔ አመራር አባል በአሜሪክ ራዲዮ ጣቢያ ላይ ወጥቶ የተናገረውን አጣቅሶ የነፀጋዬ ደብተራውን በወያኔ መረሸን አስመልክቶ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ያወጣውን ጋዜጣዊ መግለጫ ያነበብንና ጉዳዩን የምንከታተል ወገኖችን ያሳዘነንና ያስቆጣን ቢሆንም የነፀጋዬ ደብተራውን ደብዛ መጥፋት አስመልክቶ እስካሁን ከወያኔ በከፍተኛ ባለሥልጣንነት ያገለገለ ወያኔ ድፍረቱ ኖሮት መገዳላቸውን የተናገረ የለም። ነገር ግን ውስጥ ለውስጥ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚተላለፉ ዜናዎችን ለተከታተልን በቅርቡ በይፋ መነገሩን እየጠበቅን ነበር እንጂ ወያኔ አይገድላቸውም ብለን ተዘናግተን የተቀመጥንበት ጊዜ አልነበረም። አቶ ገብሩ አሥራት፣ የህዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ አንጋፋ ታጋይ፣ የቀድሞ የትግራይ ክልል ፕሬዝዳንትና የድርጅቱ ሥራ አስፈጻሚ የነበሩ፤ ወያኔ ለሁለት ከተከፈለም በኋላ የዓረና ትግራይ ለዴሞድራሲና ሉዓላዊነት መሥራችና ሊቀመንበር እንዲሁም የአንድነት ግንባር ሥራ አስፈጻሚ በቅርቡ "ሉዓላዊነትና ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ" በሚል ርዕስ የጻፉትን መጽሐፍ ለማስተዋወቅ በአሜሪካ ድምጽ የአማርኛ ዝግጅት ክፍል አቅራቢ በሆነቸው ወ/ሮ አዳነች ፍሥሃዬ የመጀመሪያው ቃለ መጠይቅ ላይ የኢሕአፓ አመራር አባላት መገደላቸውን ሲናገሩና በኢሕአፓም በኩል ከላይ በተጠቀሰው መግለጫ እንደተረዳነው ስለነፀጋዬ ደብተራው ማለት ነውና በቃለ መጠይቁ ያቀረቡትን ላደመጥን ወገኖች ወያኔዎች እነፀጋዬን የሞት ፍርድ የፈረዱባቸው ለምንድር ነው? ዛሬስ አቶ ገብሩ አሥራት በወሳኝነት አልነበርኩበትም ቢሉንምና በወያኔ አካባቢ የሚታወቀውን ነገር በድፍረት ማቅረባቸው ቢመሰገንም፣ በአሁኑ ጊዜ ይህንን የወያኔ ከፍተኛ ሚስጥር ለመናገር ለምን ፈለጉ? የእሳቸውና መሰሎቻቸው የግድያው ወሳኞች እንኳን ባይሆኑ ስለግድያው ያላቸው አስተያየትና ኃላፊነትስ ምንድር ነው ብለን መጠየቃችን አይቀርም።

**በኢሕአፓ መግለጫ ላይ ስማቸው የተዘረዘሩት፡-**

- **ፀጋዬ ገ/መድኅን (ፀጋዬ ደብተራው) - አመራር ኮሚቴ አባል፤**
- **ይስኃቅ ደብረ ጽዮን - አመራር ኮሚቴ አባል**
- **ስጦታው ሁሴን - አመራር ኮሚቴ አባል**
- **በለጠ አምሃ - አመራር ኮሚቴ አባል እንዲሁም**
- **ደሳለኝ አምሳሉ**
- **ሐጎስ በዛብህ**
- **ተክላይ ኃ/ሥላሴ**
- **አዛናው ደምሴ ( ከሱዳን ታፍኖ የተወሰደ)**

እንደሚታወቀው ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት የኢሕአፓ ታጋዮች ወያኔ በጦርነት ሚዳ ላይ በተደረገ አስቸኳይ ውሳኔ የረሸኛቸው ሳይሆን በምዕራባውያን ዕርዳት በሥልጣን ኮርቻ ላይ ከተቆናጠጠ በኋላ ለመሆኑ አቶ ገብሩም አልካዱም። በጦር ሜዳ ላይም እንኳ ቢሆን ምርኮኞችን መረሸኝ በዓለም ሕግ ያስጠይቃል። በጊዜውም አብረው ታሥረው የነበሩ ጓዶች ዛሬም በሕይወት ኖረው ሲመሰክሩ ወያኔ ለይቶ እንደወሰዳቸው የታወቀ ነው። ታዲያ ዛሬ አቶ ገብሩ አሥራት ኢፒዲአሬፍ የሞት ፍርድ ፈረደባቸው ሲሉን በምን ምክንያት? ወያኔ በጊዜው በቁጥጥር ሥር ያዋላቸው የደርግ ባለሥልጣኖች እንኳን የኋላ ኋላ በፍርድ ቤት ቀርበው ሲወሰንባቸውና አንዳንዶቹ ዛሬ ዛሬ ተፈተው የውሸት መጽሓፍ የሚጽፉበት ዕድል ሲያገኙ፣ ወያኔዎች የኢሕአፓ መሪዎችን ባስቸኳይ ለመግደል የወሰኑት ለምን ድር ነበር ብለን መጠየቃችን አይቀርም። በኢሕአፓ መግለጫ ላይ ሌሎች ስማቸው የተዘረዘሩ እንደ አበራሽ በርታ ዓይነቱ ደግሞ ራሱን የቻለ ሌላ ጥያቄ ነው። እንግዲህ አቶ ገብሩ በነሱም ላይ ፍርድ ተሰጥቶአል ካላሉን በስተቀር ማለታችን ነው። የኢሕአፓ ደብዛቸው የጠፉ ወገኖች ጉዳይ ማለትም ከላይ የተዘረዘሩትና ሌሎችንም ጨምሮ በኢትዮጵያ የሚያሳዝንና የሚያሳፍር ራሱን የቻለ ታሪክ አለው። የዓለም አቀፍ የሰብአዊ ድርጅቶች ጉዳዩ ቢቀርብላቸውም ሰምተው እንዳልሰሙ መሆናቸውና በተለየ ደግሞ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ መብት እንታገላለን የሚሉን ወገኖች እነፕሮፌሰር መስፍን መሠረቱት የሚባለው ኢሰመጉ ሳይቀር የነፀጋዬ ደብተራውን ጉዳይ ሲሸሹ፣ ሲሻቸው ምንም ዕውቅና ላለመስጠት የተመከሩ ይመስል ምክንያት ሲደረድሩ፤ ገሚሶቹ ደግሞ በሚያሳዝን ሁናቴ ድርጅቱ ይጠይቅላቸው ሲሉም ይደመጡ እንደነበር ይታወቃል። ሌላው ቀርቶ ገና ከጧቱ ወያኔ ሥር ሳይሰድ እነፕሮፌሰር አሥራት ሲታሰሩ በቁጣ ተሰልፈው የወጡ ኢትዮጵያውያን መካከል በድጋፍ የወጡ የኢሕአፓ አባላትና ደገፊዎች የነፀጋዬ ደብተራውን ስምና ምስል ይዘው በሰልፉ በመሳተፋቸው በሌላው ወገን ይደርስባቸው የነበረውን ግልምጫ ማስታወሱ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ ወያኔን ይቃወማሉ ለሚባሉ እንዲያው በአገር ቤት ያሉ ድርጅቶች ናቸውና የሚፈሩት ነገር ስላለ ነው እንኳ ቢባል በዓለም አቀፍ እንንቀሳቀሳለን፣ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ድምጽ ነን የሚሉን እንኳን ስማቸውን ማንሳት አይፈልጉም። እንዲያውም "ወያኔ የኢሕአፓን እሥረኞች እንኳ ይበላቸው!" የሚል አስተሳሰብ ያለቸውና በተዘዋዋሪ በነፀጋዬ ደብተራው ላይ ፈርደው ከወያኔ ንደሚተባበሩ እስኪያስመስላቸውና እስከ አሁኗ ሰዓት ድረስ ሰጥ ረጭ ሲሉ እስከ ዛሬ መታየቱ የሚያሳዝን የትግል ጥቁር ታሪካችን ነው። በእርግጥም ሀገሪቱን ለወያኔ አስረክበው የሸሹትን ኢሰፓዎች እንኳን አንፈርድባቸውም።

እንግዲህ በኢሕአፓና በወያኔዎች መካከል የነበረው ልዩነት ምንድር ነበር? ብለን ብንመለከት የኢትዮጵያዊነት አጀንዳና የፀረ-ኢትዮጵያዊው የገለማው የጠባብ ብሄረኝነት አባዜ ነበር። ከሁሉም በላይ ወያኔ ሻቢያ የጸነሰው መአት ስለነበርና የሻቢያን እቅድ ሊያደናቅፉ የሚችሉ ለፍርድ የሚቀርቡ የኢሕአፓ እሥረኞች ስላልተፈለጉ የሻቢያን ፍላጎት ለማሟላትም የተደረገ ግድያ ነው። ዛሬ አቶ ገብሩ አሥራት የሚያነሷቸው ነጥቦችና የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥቅም ብለው የሚያቀርቡት ራሱ ነበር ማለት ነው። እንዴ! አሲምባ ርዕሰ አንቀጽ ዛሬ አቶ ገብሩ አሥራት የሚያንሸራሽሩት የኤርትራ ጉዳይ በፌዴሬሽንና የወደብ ጥያቄ እኮ ያኔም ዛሬም የኢሕአፓ ትግል የመሠረት ድንጋይ ማለትም ዴሞክራሲያዊ ፍትሃዊ ሥርዓት መመሥረት ነው በማለት የተዋደቀበት ነው። እነፀጋዬ በወያኔ መታረዳቸው መሠረቱ ይሄው ነው ብንል ማጋነን አይሆንም። ያኔም ሆነ ዛሬ የኢሕአፓ አጀንዳ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥቅም ብቻ ነው፤ ነበርም። አንድ ወገን መጽሃፋቸውን በጋዜጣ ሲዘግብ አቶ ገብሩ በመጽሐፋቸው ደጋግመው "አሁን ቆም ብዬ ሳየው"፣"አሁን ሳጤነው"፣ "አሁን መለስ ብዬ ሳየው"፣ ይክፋም ይልማም አሁን የሚቆጩት ነገር አለ ብሎ ያቀረበውን እንስማማበት ብንል እንኳ አያሌ ጥያቄዎችን ማንሳታችን ግን አይቀሬ ነው። አቶ ገብሩ አሥራትና መሰሎቻቸው በእርግጥ ጸጸትን ያውቃሉ? ወይስ ሌላው ኢትዮጵያውያንን የመሸንገያ ውሸት? ብለን ብንጠይቅ ሊፈረድብን አይገባም። አቶ ስዬ አብራሃም እኮ ከእሥር ሲለቀቅ ወያኔን ሊጥል ተስፋ የተጣለበት ጀግና መሪያችን ተብሎለት በስደት ያለው ወገናችን ሲረገረግበት ነበርና እንዲያው የለመደች ጦጣ …..እንዳይሆንብን ለማለት ነው። በተለየ የወያኔ መሪዎች ምንም በመካከላቸው ልዩነቶች አሉን ብለው ቢካሰሱ ወያኔ እንደ ሥርዓት ኢትዮጵያንና ነፃ አወጣሃለሁ ብሎ በስሙ የሚነግድበት የትግራይ ሕዝብን የከዳ እንቅስቃሴ ስለሆነ መፍረስ ያለበት እንቅስቃሴና በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የመጣ መዓት ነው በማለት የኢትዮጵያ ሕዝብ ሊፋረደው ይገባል ሲሉ አይደመጡም። ብቻ ወያኔዎች እርስ በርስ ሲጠላለፉና ዕድላቸው አዘቅዝቆ ሲወርድ የኢትዮጵያውያንን ድጋፍ ለማግኘት የሚያቁለጨልጩበት ነገር አያጡም። የማይፈነቅሉት ድንጋይ የለምና ለጊዜውም ቢሆን የጸጸታቸው የሚመስል ነገር ተናገሩ ወይም ጻፉ ቢባል የወያኔን ወንጀልና ሚስጥር በምንም ዓይነት ሲያወጡ አይታይም። ከአቶ ገብሩ ብዙም የማንጠብቀው ለዚሁ ነው። የሚገርመው ነገር ግን በአንድነት ኃይሉ በኩል ያለው የግለሰቦች ትንንቅ ሚስጥር ሊሆን የሚገባውን ሁሉ አደባባይ አውጥተው ሲዋቀጡበትና እንታገልልሃለን የሚሉትን ተስፋ ሲያስቆርጡና ትግሉን ሲገድሉት መታየቱ ነው።

ካለፈ በኋላ ሲመረምሩት የተገነዘቡትን ሁሉን አውጥተው በድፍረት ሃላፊነትንና ዕውነታን ተገን ያደረገ ጽሁፍ አውጥተዋል የሚል ግምት ባይኖረንም አቶ ገብሩ ለጊዜው ያለቻቸውን ከወረወሩም መልካም ነው ። በተለይም እነ ፀጋዬ ደብተራው በወያኔ ስለመረሸናቸው በወያኔ ከፍተኛ ባለሥልጣን በነበር ግለሰብ በአደባባይ ሲነገር የመጀበሪያው ስለሆነ ሌሎቹም ወጥተው እንዲነግሩን እንጠብቃለን። መሠረታዊው ጥያቄአችን ግን ምንጊዜም ለምን? የሚለው ግን ተገቢና መሠረታዊ ጥያቄ ነው። የነፀጋዬ ባስቸኳይ መረሸን አንዳንዶች ሊሉን እንደሚሞክሩት ኢሕአፓና ወያኔ በጦር ይፈላለጉ ነበርና ወያኔ በኢህአፓዎች ላይ ዛሬም ሆን ያኔ ቢጨክን ይገባዋል የሚል ዓይነት ደካማ ምክንያት ኢሕአፓ በወያኔዎች ከአሲምባ ጀምሮ ጦር የተሰበቀበት ለምንድር ነው የሚለውን ጥያቄ በጥንቃቄ ላለመርመር የሚደረግ የሰነፎች ፈሊጥም እንደሚንሸራሸር የምናውቀው ነው። ለምሳሌ የኢሕአፓ የጦር መሪዎች የወያኔዎች ዓይነት የሥልጣን ኮርቻ ላይ መፈናጠጥ ዕድል ቢኖራቸው ኖሮ ወያኔዎች በኢሕአፓ መሪዎች ላይ የወሰዱት ዓይነት የችኮላ የግድያ እርምጃ ይወስዱ ነበር ወይ ብለን ብንጠይቅ መልሱ ልዩ እንደሚሆን አያጠራጥርም። ለምን ቢባል ኢሕአፓ በትግራይ ውስጥ በቀዳሚነት በወያኔ ላይ ጦር የሰበቀ ሳይሆን በተቃራኒው ወያኔዎች ለጦርነት ሲራወጡ ኢሕአፓ በውይይት ለመፍታት በርካታ ጥረቶችን ማድረጉና በጦር ሜዳ ላይም እንኳ አቅሙም ቢኖረውም ኢሕአፓ ራሱን ከመከላከል ያለፈ ወያኔን ለማጥቃት ፍላጎት እንዳልነበረው በተለያዩ እንቅስቃሴዎቹ ይታዩ እንደነበር ስለሚታወቅ ነው። ለምሳሌ እነ ፀጋዬ ይመሩት የነበረው የኢሕአፓ ጦር ኢሕአሠ በትግራይ ውስጥ ከወያኔ ጋር በቀጥታአሲምባ ርዕሰ አንቀጽ ግጭት የቆመበትን አንድ ምሳሌ አቶ ገብሩም በመጽሐፋቸው ውስጥ ቢጠቅሱትም ሙሉውን ታሪክ ያላጠቀሱትን ብንጠቅስ (በወያኔ አጫሪነት) የወያኔ አንዲት ኃይል ጦር አጋሜ ሳቢያ በሚባል ቦታ በኢሕአሠ ተከባ ልትደመሰስና ብዙ የወያኔ ወጣቶች ሊጨፈጨፉ የሚችሉበት አጣብቂኝ ውስጥ በገባች ጊዜ የነ ፀገዬ አመራር ነበር የመሸሻ ቀዳዳ በአዲ አውሊ በኩል እንዲለቀቅላትና እንድታፈገፍግ ያደረጓት። ያንን ታሪክ እኮ ዛሬም በህይወት ያለንና በቦታው የነበርን የምንመሰክረው ነው።

ዛሬ ዛሬ ወደ በኋላ ዞር ብለን ስናየው ያቺን ኃይል ልንጨርሳት ይገባ ነበር ብንልም ሳንወድ በግዳችን ግን የነፀጋዬን ብስለት፤ ታላቅነትና ሊያስከትል የሚችለውን ታሪካዊ ወቀሳ በዚያን ጊዜ አርቀው በመገንዘብ የሰጡት የመሪነት ችሎታቸውን እኛ ደግሞ ወደ ኋላ ዞር ብለን ስናስብ በአድናቆት ከፍተኛ ቦታ እንድንሰጣቸው እንገደዳለን። ወያኔዎች አቶ ገብሩ እንደሚነግሩን ከሆነ በግፍ የገደሏቸው እነ ፀገዬ ኢትዮጵያ በብዙ ትውልድ ተኪ የማታገኝላቸውን እንዲህ ያሉ መሪዎችን እንደሆነ ጠንቅቆ ማወቁ ተገቢ ነው። በወልቃይትም በወያኔ አጫሪነት በተደረገ ጦርነት እንዲሁ ዓይነት ምሳሌ ማቅረብ ይቻላል።

እዚህ ላይ ትኩረት ሊደረግበት የሚገባው ነጥብ የኢሕአፓ አመራር በዚያን ጊዜ እንደ ወያኔ በዘር እያሰባሰቡ በስሜት እየገፉ የሚያመጡዋቸውን የገጠር ወጣቶች በመጨፍጨፍ በኢትዮጵያ ውስጥ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን መመሥረት ይቻላል ብለው አያምኑበትም ነበር ። ይልቅስ አብረን በመከባበር ላይ የተመሠረተች ኢትዮጵያ ለሁሉም ትበቃለች የሚል መሠረታዊ ዕምነት ይይዛቸውና ይገድባቸው ነበር ቢባል ማጋነን አይሆንም።

ዛሬ ላይ ቆመን ታዲያ ወያኔ እነፀጋዬን ቢረሸናቸው ለምን የሚለው ጥያቄ መልሱ አንድና አንድ ብቻ ነው። ያም ኢሕአፓ የዘር ፖለቲከኞች ትጥቅ አስፈቺ ስለነበር ነው። ኢሕአፓ የሚያቸንፈው ሕዝቡ የሥልጣኑ ባለቤት ሲሆን ብቻ ነው የሚለው ፍልስፍና ለሁሉም ለሥልጣን ለሚራወጡ፣ የዛሬዎቹም የትላንቱም ነፍሰ ገዳዮች ማርከሻ የሕዝብ ጠበቃ መሆኑ ብቻ ነበር፣ ዛሬም እንዲሁ።

## ለማጠቃለል፡-

በወያኔና በኢሕአፓ መካከል ብዙ ልዩነቶች አሉ። ወያኔ የተጣመመ ጥላቻውን በኢትዮጵያ ላይ ለማንሰራፋት የፈጸማቸው ደባዎች ብዙ ናቸው። የፈጸማቸው ወንጀሎችና ውሸቶች ተቆጥረው አያልቁም። ወያኔ ኢሕአፓን የወጋው በትግራይ ስለንተንቀሳቀሰ ብቻም አልነበረም። ወያኔ የሻቢያ ሥራ አስፈጻሚ ሆኖ የተጸነሰ ለመሆኑ አቶ ገብሩም በመጽሐፋቸው አልካዱትም። ከሌላው የኤርትራ ነፃ አውጪ ግንባር ከጀብሃ ጋር እኮ ሻቢያን ለመርዳት ብዙ የትግራይ ወጣቶችን ወያኔዎች አስጨርሰዋል። የወያኔ ታሪክ የትግል ልዮነቶችን በጠረጴዛ ዙሪያ ከመፍታት ይልቅ በጦር ለመፍታቱ አቶ ገብሩ እንደፃፉትም በትግራይና ባካቢቢው ይንቀሳቀሱ ከነበሩ ድርጅቶች ጋር ያደረጓቸው ጦርነቶች ምስክሮች ናቸው። ወያኔዎች ነጻ አናወጣዋለን ላሉት የትግራይ ሕዝብ ለድርቅ የተላከለትን ምግብ ሳይቀር ለራሳቸው ጦር መሠሪያ መግዣ ሸጠውታል። ፈላሻ ስደተኞችን ቸብችበዋል። የሻቢያን የኮሎኒያል ጥያቄ ከጽነሰታቸው ጀምረው ደግፈው በመጨረሻም ፈርመው የኤርትራን ሕዝብ ለባርነት ዳርገዋል። ሀገር ከድተዋል። ዛሬም ኢትዮጵያን እያራቆቱና እየቸበቸቧት ነው። ወያኔዎች የነበሩ ሲናዘዙ ታዲያ ሁሉን ፍርጥርጥ አድርገው የተሸረበውን ሁሉ ቢሆን ዕውነት ይሆናል። ተራራን ያንቀጠቀጠ ውሸት ቢከመር ዕውነትን አይቀብረውም። አቶ ገብሩ አሥራት ወያኔ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ እየፈጸመና የፈጸመውን ወኝጀል የሚያውቁትን ሁሉ በመጽሐፋቸው ዘርዝረው ያቀርባሉ ብለን ባንጠብቅም እውነትና ንጋትአሲምባ ርዕሰ አንቀጽ እያደር እየጠራ መሄዱ አይቀርምና ስለ ዕውነት በዕውነት ከተነጋገርንና አጀንዳችን ኢትዮጵያዊነት ከሆነ ሁላችንም ላጠፋነው በመጨረሻ የሚጠይቀን ፍርዱን የሚሰጥ የምንታገልለት ሕዝብ መሆኑን አጥብቀን ካመንን የሚያስፈራን ነገር አይኖርም። እንደ አቶ ገብሩ አሥራት ዓይነቱ የዛሬዎቹም ሆነ የቀድሞዎቹ የወያኔ ቱባ ባለሥልጣናትና መሥራቾች የወያኔ እንቅስቃሴ በሀገራችን ላይ ያደረሰውን ጥፋትና ክህደት ከልባቸው ተቀብለውት ከሆነ ስህተት ነበር ብቻ በቂ አይሆንም። በዚህ ከሃዲ ድርጅት ውስጥ መሳተፋቸውን በመጸጸት አቅርበው ይህን እንቅስቃሴ ማውገዝ ይጠበቅባቸዋል። ሰልፋቸውንም ወያኔን ከነሰንኮፉ ነቃቅለው በምትኩ ፍትሃዊ ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመገንባት ከሚታገሉ ወገኖች መካከል መሆን ይገባዋል። **<u>በኛ በኩል እነ ፀጋዬ የተገደሉት ኢትዮጵያዊ አጀንዳ ይዘው በመዋደቃቸው ብቻ ነው። ስለሆነም ለዘለዓለም ሕያው ኢትዮጵያዊ ሰማዕታት ናቸው።</u>**

የአሲምባ ድረ-ገጽ ዝግጅት ክፍል

ኢትዮጵያዊነት ያለጥርጥር በትግላችን ያቸንፋል